በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የግዥና ንብረት አስተዳደሩ ኢኮኖሚያዊ ውጤታማ እና ቀልጣፋ መሆኑን በተመለከተ የተከናወነ ክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

ሰኔ 2009 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

ማውጫ

ማውጫ i
መግቢያ 3
የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አመሰራረት 3
የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ራእይ እና ተልዕኮ 4
ራዕይ 4
ተልእኮ 4
የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ዓላማ 4
የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አደረጃጀት እና የሰው ኃይል 5
የባንኩ አደረጃጀት 5
የንግድ ባንኩ የፋይናንስ ምንጭ 5
የኦዲቱ ዓላማ 6
የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ 6
የኦዲት አካባቢ (Potential Audit Area) 7
የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች እና የመመዘኛ መስፈርቶች 7
በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የግዥና ንብረት አስተዳደር የአሰራር ሥርዓት መግለጫ /System description/ 8
ክፍል ሁለት 9
ግኝቶች 9
2.1 የባንኩን የግዥ አፈፃፀም ወጪ ቆጣቢ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ ስለመሆኑ፣ 9
የባንኩ የግዥ መመሪያ ማዘጋጀቱን በተመለከተ፣ 9
የግዥ አመታዊ ዕቅዱ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፣ 10
ሰንጠረዥ 2 ፡- የሶስት ዓመት የግዥ በጀት እና ስራ ላይ የዋለ ንጽጽር 11
የግዥ ቴክኒካል ፍላጎት መግለጫ በባለሙያ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ 13
ጨረታዎች በተያዘላቸው ጊዜ የሚጠናቀቁ መሆናቸውን በተመለከተ፣ 16
የግዥ ቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ የሚያዘጋጅውና የሚገመግመው ባለሙያን በተመለከተ፣ 18
ግዥዎች በመመሪያው መሰረት በውድድር መፈጸማቸውን በተመለከተ፣ 19
ሰንጠረዥ 3፡- ያለበቂ ምክንያት በውስን ጨረታ የተገዙ የግዥ ሰነዶች 22
ግዥ የማፅደቅ ስራ የግዥ አፅዳቂ ቡድን የሚከናወን መሆኑን በተለመከተ፣ 24
2.2 የባንኩ ንብረት አስተዳደር ወጪ ቆጣቢ ውጤታማና ቀልጣፋ ስለመሆኑ፣ 25
2.2.1 የንብረት አያያዝ እና አጠቃቀም ስርዓት መኖሩንና ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፣ 25

በባንኩ የሚገዙ ዕቃዎች በወቅቱ ማሰራጨትን በተመለከተ፤ 25
የንብረት ርክክብ ሥርዓት መኖሩን በተመለከተ፤ 27
ለባንኩ ንብረቶች የጥገና ስርዓት መኖሩን እና ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፤ 28
በባንኩ መጋዘን ውስጥ የንብረቶችን ከፍተኛና ዝቅተኛ የዕቃ መጠን የተወሰነ መሆኑን በተመለከተ፤ 30
አገልግሎት የሚሰጡ እና የማይሰጡ ንብረቶች አቀማመጥን በተመለከተ፤ 32
በባንኩ በዕዳ የተወረሱ ንብረቶችን አስተዳደርን በተመለከተ፤ 34
2.2.2 የንብረት አወጋገድ ስርዓት መኖሩንና ተግባራዊ ስለመሆኑ፤ 38
መወገድ የሚገባቸው የባንኩ ንብረቶችን በተመለከተ፤ 38
2.3 የባንኩ የግዥና ንብረት አስተዳደርን በተመለከተ የመረጃ አያያዝ ስርዓት መኖሩን መገምገም. 40
በባንኩ ለሚከናወኑ ግዥዎች የገበያ ጥናት መከናወኑን በተመለከተ፤ 40
የባንኩን የዕቃ አቅራቢዎች ዝርዝር ወቅታዊ መደረጉን በተመለከተ፤ 42
ወቅታዊ የሆነ የመረጃን ልውውጥንና አደረጃጀትን በተመለከተ፤ 44
ክፍል ሶስት 46
የመደምደሚያ ሀሳቦች 46
ክፍል አራት 48
የማሻሻያ ሀሳቦች 48
አባሪ 1 የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative Criterias) 52
አባሪ 2፡ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ድርጅታዊ መዋቅር 54
አባሪ 3፡ ማስረጃ ያላሟሉ ተጫራቾችን የሚያሳይ ሰንጠረዥ 55
አባሪ 4፡ የአሰራር ስርዓት ስዕላዊ መግለጫ 58
አባሪ 5፡ በቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ (ስፔስፊኬሽን) መሰረት ስለመሆናቸው በተገቢው ባለሙያ ስለመረጋገጡ የሚያስረዳ ማስረጃ ያልቀረበላቸው ግዥዎች 59

ክፍል አንድ

መግቢያ

1. በሁለተኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መሰረት ሀገሪቱ መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገሮች ተርታ ለመሰለፍ በምታከናውነው ግዙፍ እና ዘርፈ ብዙ የልማት እንቅስቃሴዎችን በፋይናንስ ከመደግፍ አንጻር ባንኮች ጉልህ አስተዋፅኦ እያደረጉ ይገኛሉ፡፡ በዚህም መሰረት የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የዘረጋውን የአሰራር ስርዓት መተግበርና አጠናክሮ መቀጠል ያለበት ከመሆኑም በላይ መንግስት ካስቀመጠው ሀገራዊ የልማት ግብ አንፃር ጠንካራና ተወዳዳሪ የመንግስት ፋይናንስ ተቋም መኖሩ የልማት ግቡን በተቀመጠለት ጊዜ ገደብ ተግባራዊ እንዲሆን ለማስቻል የጎላ ፋይዳ ይኖረዋል፡፡ ባንኩ ከዘረጋቸው የአሰራር ስርዓቶች ውስጥ አንዱና ዋነኛው የግዥና ንብረት አስተዳደር ነው፡፡ በመሆኑም የባንኩ የግዥና ንብረት አስተዳደር ስርዓት ወጪ ቆጣቢ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ ሁኔታ ተግባራዊ እንዲሆን ይጠበቃል፡፡

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አመሰራረት

2. የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በኢትዮጵያ የመጀመሪያውና ትልቁ የንግድ ባንክ ሲሆን እ.አ.አ. በ1942 የመንግስት ባንክ ሆኖ በአዋጅ ተቋቋመ፡፡ እ.አ.አ. በሚያዝያ በ1943 በሁለት ቅርንጫፎች የባንክ አገልግሎት ሥራውን ጀመረ፡፡ በወቅቱ ባንኩ የወረቀት ገንዘብና ሳንቲሞችን የገንዘብ ሚኒስቴር ወኪል በመሆን ለሀገሪቱ ጥቅም ላይ እንዲውል የማድረግ ስልጣን ነበረው፡፡

3. ባንኩ ከኢትዮጵያ ውጭ እ.አ.አ. በ1958 በሱዳን የኢትዮጵያ የመንግስት ባንክ ቅርንጫፍ የተከፈተ እና በጊዜ ሂደትም ቅርንጫፎቹን እያሳደገ የመጣ መሆኑ፣ እ.አ.አ. በ1950 በጅቡቲ ቅርንጫፉን እንዳቋቋመ በአሁኑ ወቅትም በሁለቱም ሀገሮች ባንኩ አገልግሎቱን እየሰጠ እንደሚገኝ ታውቋል፡፡ በደቡብ ሱዳን እ.አ.አ እስከ 2009 አራት ቅርንጫፎችን ከፍቶ እየሰራ ይገኛል፡፡

4. በኢትዮጵያ መንግስት ባለቤትነት የሚተዳደሩ ሦስት ባንኮች የነበሩ ሲሆን እነዚህም የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ፣ የኢትዮጵያ ልማት ባንክ እና የኮንስትራክሽንና ቢዝነስ ባንክ ነበሩ፡፡ ነገር ግን እ.አ.አ በሚያዝያ 1/2016 የኮንስትራክሽንና ቢዝነስ ባንክ ከኢትዮጵያ

ንግድ ባንክ ጋር ተቀላቅሎ እየሰራ ይገኛል፡፡ በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ከ1150 በላይ ቅርንጫፎች አሉት፡፡

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ራእይ እና ተልዕኮ

ራዕይ

✓ እ.አ.አ በ2025 በአለም ተወዳዳሪ ከሆኑ ንግድ ባንኮች አንዱ መሆን ነው፡፡

ተልእኮ

✓ ከፍተኛ ተነሳሽነት ሙያዊ ብቃትና ጥሩ ሥነ ምግባር ያላቸው ሰራተኞች እና ዘመናዊ የባንክ ቴክኖሎጂን በመጠቀም አለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ የፋይናንስ አገልግሎት መስጠት፣

✓ ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ብሔራዊ የልማት ስራዎች በመደገፍ የባለድርሻ አካላትን ፍላጎቶች ለማርካት በቁርጠኝነት መስራት፣

✓ የህብረተሰቡን ያልተገደበ አመኔታ ማትረፍ ለስኬታማነት መሠረት መሆኑን፣

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ዓላማ

5. የኢትዮጵያ ንግድ ባንክን ለማቋቋም በወጣው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 202/1987መሠረት የሚከተሉት ዓላማዎች ተሰጥተውታል፤

✓ የቁጠባ፣ በተጠየቀ ጊዜ የሚከፈልና የጊዜ ገደብ ያለው ተቀማጭ ገንዘብ መቀበል፣

✓ በኢትዮጵያ ውስጥ ወይም በውጭ ተከፋይ የሚሆኑ የሃዋላ ወረቀቶች፣ የገንዘብ ሰነዶችና የተስፋ ሰነዶች ማውጣት፣ መቀበል፣ በቅናሽ መውሰድ፣ መግዛትና መሸጥ፣

✓ የንግድ መተማመኛ ብድር ደብዳቤዎች መስጠት፣

✓ የአጭርና የመካከለኛ ጊዜ ብድሮችን መስጠት፣ ከተወሰነ ጣሪያ ሳያልፍ የረጅም ጊዜ ብድሮችን መስጠት፣

✓ የውጭ ሀገር ምንዛሪ መግዛትና መሸጥ፣

✓ መንግስት፣ የግል ድርጅት ወይም ማንኛውም ሰው የሚያወጣቸውን የሚተላለፉ የገንዘብ ሰነዶችና የዋስትና ሰነዶች መግዛትና መሸጥ፣

✓ ሰነዶችን ጌጣጌጦችንና ሌሎች ዋጋ ያላቸውን ነገሮች በአደራ መቀበልና ማኖር፣

✓ ቼኮችና የመንገደኛ ቼኮች ማውጣትና በጠቅላላው በቼኮች መስራት፣

- ✓ ለሰዎች ወኪል ሆኖ ገንዘቦችና አክሲዮኖች መሸጥ፣ በማናቸውም ኢንቨስትመንት የአክሲዮን ድርሻ በመያዝ መሳተፍ፣
- ✓ ሌሎች የተለመዱ የንግድ ባንክ ሥራዎችን ማከናወን፣

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አደረጃጀት እና የሰው ኃይል

የባንኩ አደረጃጀት

6. የኢትዮጵያ ንግድባንክ በአንድ ፕሬዝዳንት የሚመራ ሲሆን ስምንት ምክትል ፕሬዝዳንቶች (ዓለም አቀፍ ንግድ አገልግሎት፣ ብድር አስተዳደር፣ የሰው ሀይል አስተዳደር፣ የደንበኞች ሂሳብና እንቅስቃሴ አገልግሎት፣ የመረጃ ስርዓት፣ የብድር ግምገማና ፖርትፎሊዮ አስተዳደር፣ የፋሲሊቲዎች አስተዳደር እና ፋይናንስ) እና አራት ቺፎች (ዋና የህግና የብድር መገገሚያ መኮንን፣ ዋና የሪስክና ኮምፕሊያንስ መኮንን፣ ዋና የውስጥ ኦዲተር እና ዋና ቢዝነስ ዴቬሎፕመንት መኮንን) አሉት፡፡ የባንኩ ፕሬዝዳንት ተጠሪነቱ ለዳይሬክተሮች ቦርድ ነው፡፡ ከሰባቱ ምክትል ፕሬዝዳንቶች አንዱ ፋሲሊቲ ማኔጅመንት ነው፡፡ በፋሲሊቲ ማኔጅመንት ምክትል ፕሬዝዳንት ስር የዕቃ አቅርቦት ዳይሬክቶሬት፣ ህንፃና ግንባታ ስራ አመራር ዳይሬክቶሬት፣ በዕዳ የተወረሱ ንብረቶች አስተዳደር፣ ትራንስፖርት አስተዳደር እና አርካይቭ ይገኛሉ፡፡ ለዝርዝር መረጃ የባንኩ ድርጅታዊ መዋቅሩ **በአባሪ 2** ተያይዟል፡፡

የሰው ኃይል

7. ባንኩ እ.አ.አ. እስከ መጋቢት 16/2017 ድረስ ባለው መረጃ መሰረት 28208 ሰራተኞች ያሉት ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ ወንድ 21240 (75%) ሴት 6968 (25%) በድምሩ 28208 ሰራተኞች አሉት፡፡ ፕሮፌሽናል ወንድ 19693 ሴት 6242 ድምር 25935 እንዲሁም ፕሮፌሽናል ያልሆኑ ወንድ 1503 ሴት 715 ድምር 2218 በጠቅላላው 28150 ሠራተኞች አሉት፡፡

የንግድ ባንኩ የፋይናንስ ምንጭ

8. የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 202/1987 የተሰጠውን ተግባር ለማከናወን ከሚገኘውዓመታዊ ትርፍ በጀቱን የሚመድብ ሲሆን ከ2006 እስከ 2008 በጀት ዓመት ድረስ የተመደበው በጀት እና ስራ ላይ የዋለው ወጪ እንደሚከተለው በሰንጠረዥ አንድ ተመልክቷል፡፡

በጀት ዓመት	አጠቃላይ የባንኩ በጀት	ስራ ላይ የዋለ አጠቃላይ በጀት	ሥራ ላይ የዋለው በጀት በመቶኛ
2013/14 (2006)	1,794,200,000	1,084,086,000	60.4
2014/15 (2007)	2,875,948,300	1,570,580,700	54.6
2015/16 (2008)	4,808,970,000	3,751,334,000	78

የኦዲቱ ዓላማ

9. ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በአዋጅ ቁጥር 982/2008 በተሰጠው ስልጣን እንዲሁም በዓለም ዐቀፍ የክዋኔ ኦዲት ስታንደርድ እና በኢትዮጵያ የክዋኔ ኦዲት ማንዋል መሰረት ነው፡፡ የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የግዥና ንብረት አስተዳደሩወጪ ቆጣቢ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ በሆነ መልክ እየተከናወነ መሆኑን በመገምገም የሚታዩ ችግሮችን በመለየት ችግሮቹን ለማስወገድ ወይም ለማቃለል ሊተገበሩ የሚችሉ የማሻሻያ ሃሳቦችን ለማቅረብ ነው፡፡

የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ

10. ዝርዝር ኦዲቱ የተከናወነው በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የንብረት ግዥና አስተዳደር ወጪ ቆጣቢ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ በሆነ መልክ እየተከናወነ መሆኑን ሊያሳዩ የሚችሉ መረጃዎችን በመከለስና ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የባንኩ ዳሬክቶሬቶችን፣ የዲስትሪክት እና የቅርንጫፍ ስራ አስኪያጆች ጋር ቃለ-መጠይቅ በማድረግ እንዲሁም የባንኩ የንብረት መጋዘኖችን በማየት ነው፡፡ በዚህም መሰረት በዕቃ አቅርቦት ዳይሬክቶሬት፣ በመጋዘን አስተዳደር፣ በዕዳ የተያዙ ንብረቶች አስተዳደር፣ በሂሳብና ማስታረቅ ዳይሬክቶሬት፣ በህንፃና ግንባታ ዳይሬክቶሬት፣ በግንባታ ፕሮጀክት ቢሮ፣ በንብረት አስወጋጅ ኮሚቴ፣ በአዲስ አበባ በሚገኙ አራቱ ዲስትሪክቶችና በስራቸው ባሉ በናሙና የተመረጡ ቅርንጫፎች፣ በክልል በሚገኙ ሁለት ዲስትሪክቶችና የተመረጡ ቅርንጫፎች በተጠቀሱት የኦዲት ዘዴዎች ማስረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ ኦዲቱ የሚሸፍነው ከ2006 እስከ 2008 በጀት ዓመት ያሉትን ሶስት አመታት ነው፡፡

የኦዲት አካባቢ (Potential Audit Area)

11. ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አከባቢ (Potential Audit Area) በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የንብረት ግዥና አስተዳደር በብቃት፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ በሆነ ሁኔታ እየተከናወነ መሆኑን መገምገምነው፡፡

የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች እና የመመዘኛ መስፈርቶች

የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues)

12. ከላይ በተገለጸው የኦዲት አካባቢ ስር ሶስት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues) እና ሁለት ንዑስ የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች (Sub audit Issues) ተለይተዋል፡፡ እነርሱም-

1. የባንኩ የግዥ አፈፃፀም ወጪ ቆጣቢ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑን መገምገም
2. የባንኩ ንብረት አስተዳደር ወጪ ቆጣቢ ውጤታማና ቀልጣፋ መሆኑን መገምገም፣
    - ✓ የንብረት አያያዝ እና አጠቃቀም ስርዓት መኖሩንና ተግባራዊ መሆኑን መገምገም፣
    - ✓ የንብረት አወጋገድ ስርዓት መኖሩንና ተግባራዊ መሆኑን መገምገም፣
3. የባንኩ የግዥና ንብረት አስተዳደርን በተመለከተ የመረጃ አያያዝ ስርዓትና በዘርፉ ለተሰማሩ ሰራተኞች የስልጠና ስርዓት መኖሩን መገምገም፣

ናቸው፡፡

የኦዲት መመዘኛ መስፈርት (Evaluative criteria)

13. በኦዲት ቡድኑ ለተመረጡት ሶስት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issue) እና ሁለት ንዑስ የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች (Sub audit Issues) ለመመዘን የሚረዱ 30 የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative criteria) ተዘጋጅተዋል፡፡ እነዚህን የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች ለማዘጋጀት መሠረት የሆኑት የባንኩን የግዥ አፈፃፀም መመሪያ፣ በአገልግሎት ተግባር ላይ የማይውሉ ንብረቶችን ለማስወገድ የሚያስችል መመሪያ እና ሌሎች የተለያዩ መመሪያዎችና ፕሮሲጀሮች፣ በባንኩ በግዥ ላይ የተከናወነ ደሰሳ ጥናት፣ የባንኩ የ5 አመት ስትራቴጅክ ዕቅድ፣ መልካም የሥራ

ተሞክሮዎች እና የባንኩ የመረጃ ድህረ ገጾች /web site/ ናቸው፡፡ የተዘጋጁት መመዘኛ መስፈርቶች በባንኩ አስተያየት እንዲሰጥበት ተደርጓል፡፡ የመመዘኛ መስፈርቶቹ በአባሪ 1 ተያይዘዋል፡፡

በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የግዥና ንብረት አስተዳደር የአሰራር ሥርዓት መግለጫ /System description/

14. ግዥ የሚከናወነው በቅድሚያ የተጠቃሚ አካላትን ፍላጎት በማሰባሰብ ሲሆን በቀጣይ በተሰበሰበው ፍላጎት ላይ በመመስረት ንብረቱንና አገልግሎቱን እንዴት መግዛትና ማቅረብ እንደሚቻል ከሌሎቹ የሥራ ክፍሎች ጋር በጋራ ዕቅድ ይታቀዳል፡፡ የተፈለገው ንብረት ወይም አገልግሎት በትክክል እንዲቀርብ የተዘጋጀው ስፔስፊኬሽን ለአቅራቢው ግልፅ እንዲሆን ይደረጋል፡፡ ጨረታ በማውጣት በተቀመጠው ስፔስፊኬሽን እና የጨረታ ኮሚቴው ባስቀመጠው አናላሲስ መሰረት ጨረታው ይገመገማል እንዲሁም የአቅራቢዎች የማቅረብ ችሎታና የቴክኒክ ግምገማው ይታያል፡፡

15. የጨረታ ግምገማው አልቆ አሸናፊው ከታወቀ በኋላ አቅራቢው ንብረቱን ወይም አገልግሎቱን እንዲያቀርብ ትዕዛዝ ማቅረብ ወይም ውል መዋዋል ቀጣዩ ሂደት ነው፡፡ የውል ስምምነቱ ዋጋ፣ ስፔስፊኬሽን፣ መጠን፣ የማቅረቢያ ቦታና ጊዜ፣ ውሉ ቢቋረጥ የሚከተሉ ቅጣቶችን እና ሌሎች ተያያዥ ነገሮችን እንዲያካትት ይደረጋል፡፡ በመቀጠል የተገዙት ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች የኮንትራት ስምምነቱ በሚያዘው መሰረት መግባታቸውን ወይም አገልግሎቱ መሰጠቱን የግዥ ክፍሉ ያረጋግጣል፡፡ ዕቃው ወደ መጋዘን ከገባ በኋላ ግዥ ክፍሉ አስፈላጊውን መረጃ ለፋይናንስ ክፍል በመስጠት ክፍያው ለአቅራቢው እንዲፈፀም ይደረጋል፡፡ በመጨረሻም የተገዙት ዕቃዎች በመጋዘን በማስቀመጥ ጥያቄውን ላቀረቡ ዲስትሪክቶች ወይም ቅርንጫፎች በወቅቱ እንዲከፋፈል ይደረጋል፡፡ የአሰራር ስርዓቱ ስዕላዊ መግለጫ በአባሪ 4 ተያይዟል፡፡

ክፍል ሁለት

ግኝቶች

2.1 የባንኩን የግዥ አፈፃፀም ወጪ ቆጣቢ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ ስለመሆኑ፤

የባንኩ የግዥ መመሪያ ማዘጋጀቱን በተመለከተ፤

16. የመንግስት የግዥ አፈፃፀም መመሪያን መሰረት በማድረግ ባንኩ የራሱን የግዥ መመሪያ ሊያወጣና በሚመለከተው አካል በማፀደቅ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

17. በኦዲት ወቅት እንደተረጋገጠው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የራሱ የሆነ የግዥ መመሪያ አዘጋጅቷል፡፤ በባንኩ የግዥ መመሪያ ላይ የረጅም ግዥ ውል መፈጸም እንደሚቻል ተጠቅሷል፡፡ ይሁን እንጂ መመሪያው በረጅም ጊዜ ውል ግዥ ለመፈጸም የሚቻለው ምን አይነት ሁኔታዎች ሲሟሉ እንደሆነ አይገልጽም፡፡

18. ስለሁኔታው የባንኩ ኃላፊዎች ተጠይቀው የረጅም ጊዜ አቅርቦት ወይም የማዕቀፍ ስምምነት ለመፈፀም የሚያስችሉ መርሆችና ቅድመ ሁኔታዎች በመመሪያው ክፍል አራት አንቀፅ 25 እና አንቀፅ 29.2 ላይ በዝርዝር እንደተገለፁ እንዲሁም የረጅም ጊዜ አቅርቦት ሊገባላቸው የሚችሉ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ዝርዝር በግዥ መመሪያው ላይ ተዘርዝረው እንደተቀመጡ በቀረበላቸው ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል፡፡

19. ኃላፊዎቹ ይህን ቢሉም የግዥው ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ፣ በቴክኖሎጂ ለውጥ ምክንያት ሥራ ላይ ለማዋልም ሆነ የመጀመሪው ዋጋ ላይ ተጽዕኖ ማስከተል አለማስከተላቸው በመመሪያው ላይ በግልፅ ያልተቀመጠ በመሆኑ እና የረጅም ጊዜ ውል የተገባባቸው ግዥዎች ከባንኩ ስትራቴጂ ዕቅድ ጋር ስለመያያዛቸው ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ መረጃ ባለመቅረቡ የተሰጠውን አስተያየት ለመቀበል ይከብዳል፡፡

20. የረጅም ጊዜ ውል ስምምነት ግዥዎችን ለመፈጸም፣ ለባንኩ ኢኮኖሚያዊ ወይም የተለየ ጥቅም የሚያስገኝ መሆኑ በግልጽ መስፈርት ተዘጋጅቶ ካልተከናወነ ባንኩ በረጅም ጊዜ ውል ስምምነት በመፈጸም የረጅም ጊዜ ውል ስለተገባ ብቻ

ቴክኖሎጂያቸው የተቀየሩ ዕቃዎችን እንዲገዙ ለማድረግ በር ስለሚከፍትና ሥራ ላይ የማይውሉ ዕቃዎች እና ንብረቶች በመገዛት ለብክነት ሊዳርግ ይችላል፡፡

የግዥ አመታዊ ዕቅዱ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፤

21. ባንኩ አመታዊ የግዥ ዕቅድ ሊያዘጋጅ ይገባል፡፤ ዕቅዱም ሲዘጋጅ የግዥ ፍላጎት በግዥ ዕቃዎች አይነት፣ ብዛት እና የጥራት ደረጃ ከሁሉም የሥራ ክፍሎች፣ ዲስትሪክቶች እና ቅርንጫፎች በመሰብሰብ እና በመተንተን እና በመጋዘን ያሉትን ንብረቶች ከግምት ውስጥ በማስገባት መሆን ይገባዋል፡፤ የተዘጋጀው አመታዊ የግዥ ዕቅድ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

22. ባንኩ ዓመታዊ የግዥ ዕቅድ የሚያዘጋጅ መሆኑ ታውቋል፡፡ ነገር ግን የባንኩ ግዥዎች በተዘጋጀው የግዥ እቅድ መሰረት ተግባራዊ ስለማይደረጉ፡

- የባንኩ ዲስትሪክቶች እና ቅርንጫፎች የሚጠይቁት ዕቃ በእቅዱ መሰረት በወቅቱ ግዥ ተፈፅሞ እንደማይደርሳቸው አልፎ አልፎም ከዓመት በላይ የሚቆይ መሆኑ፣
- ዕቅድ ሲዘጋጅ በመጋዘን ያለው ክምችት ከግምት ውስጥ ገብቶ ባለመታቀዱ በጨረታ ቁጥር 09/2015/16 ኦሜዳድ ኃ/የተ/የግ/ኩባንያ በሁለት ዓይነት ዕቃዎች ማለትም Filling cabinet with 4 drawers ብዛት 1,480 እና Filling cabinet with 2 drawers ብዛት 170 አጠቃላይ በብር 6,110,697.50 ጨረታውን ድርጅቱ ሙሉ በሙሉ አሸናፊ ሆኖ ዉል ስምምነት ከተፈራረሙ በኋላ በተደረገው ማጣራት በግምጃ ቤት ያለው ዕቃ ለበጀት ዓመቱ በቂ ነዉ በሚል ምክንያት ግንቦት 09 ቀን 2008 ዓ.ም በቁጥር ተሥዕግአ/ውመ/680/16 በተፃፈ ደብዳቤ ግዥው የተሰረዘ መሆኑን
- ባንኩ በ2013/14-2015/16 በጀት አመታት የግዥ ዕቅዱን ያሳካው በ2013/14 47 ከመቶ፣ የ2014/15 58 ከመቶ እና የ2015/16 56 ከመቶ መሆኑ፣ (የባንኩ የሶስት ዓመት የግዥ ዕቅድ ክንውን ከዚህ በታች በሰንጠረዥ ተመልክቷል)

በጀት ዓመት	የታቀደው ብር	ክንውን ብር	ክንውን(%)
2013/14	1,161,929,000	543,063,000	46.74
2014/15	1,238,800,000	716,879,000	57.87
2015/16	1,810,295,000	1,014,896,000	56.01

ሰንጠረዥ 2 ፡- የሶስት ዓመት የግዥ በጀት እና ስራ ላይ የዋለ ንጽጽር

- ግዥው ከተከናወነ በኋላ ተጨማሪ ዕቃ ሲያስፈልግ ካሸናፊው ተጫራች 20% ያልበለጠ ዕቃ ጨምሮ መግዛት እንደሚቻል በግዥ መመሪያው አንቀፅ 27 ንዑስ አንቀፅ 27.1.17 ላይ የተገለጸ ቢሆንም ከመመሪያው ውጭ በብልጫ የሚገዛ መሆኑ፣
  - በጨረታ ቁጥር 16/2014/15 ማስታወቂያዉ ላይ የተገለፀዉ Cash box ብዛት 2206 ሲሆን ከአሸናፊዉ አቅራቢ ህይሰን ዌብጌት ብዛታቸው 2758 የሚሆኑ Cash box በብር 6,591,620 የተገዙ ሲሆን ይህም የእቃው ብዛት መመሪያው ላይ ከተጠቀሰው 2% በብልጫ የተገዛ መሆኑ፣
  - በጨረታ ቁጥር 13/2014/15 ብር 9,356,790.03 ዋጋ ያለው እና በማስታወቂያ ላይ የተገለፀዉ የእቃ ብዛት dixon shelve 750፣ lateral filling cabinet with 4 shelve 138፣ filling cabinet with 2 drawers 128 እና filling cabinet with 4 drawers 1086 ሲሆን አሸናፊዉ አቅራቢ ብራይት ያቀረበዉ በቅደም ተከተል ብዛት 1288፣ 174፣ 198፣ 1591 በመሆኑ በየዕቃዎቹ በቅደም ተከተል 52%፣ 6%፣ 34% እና 26% መመሪያው ከጠቀሰው በላይ በብልጫ የተገዛ መሆኑ፣

በኦዲት ወቅት በናሙና ተመርጠው የታዩት ዲስትሪክት እና ቅርንጫፍ ስራ አስኪያጆች በቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ የገለጹ እና ከተከለሰው መረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡

23. ስለጉዳዩ የባንኩ ፋሲሊቲ አስተዳደር የስራ ኃላፊዎች ባንኩ ስትራቴጅክ እቅድ ቢኖረውም የግዥን ጉዳይ በዝርዝር በስትራቴጅክ ዕቅዱ ላይ ማሳየት እንደማይቻል ሆኖም ግን በየግዥ ክፍሉ ባላንስድ ስኮር ካርድ የሚዘጋጅ መሆኑን እና በተለያዩ ምክንያቶች ግዥዎች በእቅዱ መሰረት ተግባራዊ እንደማይሆን በቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ ላይ በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

24. ስለሁኔታው የባንኩ የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው፡-

- የግዥ ስትራቴጂክ ዕቅድ የተዘጋጀ እና እየተተገበረ ያለ ሲሆን በጥናቱ ላይ የተቀመጠው የግዥ ስትራቴጂክ ዕቅድ የለውም የሚለው ጥናቱን ተመርኩዞ አለመከለሱን ለማመልከት መሆኑን፣

- ግዥዎች የሚዘገዩት ስራዎች በቅብብሎሽ በመሰራታቸው ምክንያት በመሆኑና ይህን የባንኩ ቁልፍ ችግር ለመቅረፍ መፍትሄ እንዳስቀመጠለትና የግዥ Standard Delivery Time ተዘጋጅቶ በ2009 ዓ/ም ተከልሶ የፀደቀው የግዥ መመሪያ አካል መደረጉን፤ የጨረታ ቁጥር 09/2015/16 ግዥን በተመለከተ የበጀት አመቱ ሊጠናቀቅ የቀረው ጊዜ በጣም አነስተኛ በመሆኑና በግምጃ ቤትም ያለው ክምችት እስከ ቀጣዩ የበጀት ዓመት የጠያቂያችን ፍላጎት የሚሸፍን ሆኖ በመገኘቱ መሆኑን፣ የግዥ ዕቅዱ በበቂ ጥናትና በባንኩ ዕድገት በመነጨ የግዥ ጥያቄዎች ላይ ተመስርቶ ቢዘጋጅም የግዥ ዕቅድ አፈፃፀም አናሳ መሆን ባንኩ ያለበትን የአፈፃፀም ክፍተት የሚያሳይ መሆኑን
- ግዥ ከተከናወነ በኋላ ለሚደረግ ተጨማሪ ግዥ ግዥው በግልጽ ጨረታ የተከናወነ ከሆነ ቀደም ሲል ከታዘዘው ዕቃዎች ወይም አገልግሎት ግዥ መጠን እስከ 25% ድረስ ጭማሪ ማድረግ እንደሚቻል በግዥ መመሪያው አንቀጽ 24.1.1 "ሀ" ላይ የተገለፀ እና የግዥ መመሪያ አንቀጽ 27.1.17 ላይ ባንኩ ከአሸናፊው ተጫራች ጋር ውል ከመፈረሙ በፊት እስከ 20% መጨመር ወይም መቀነስ እንደሚችል የተገለፀ ሲሆን ከላይ የተገለጹትን አንቀጾች በማገናዘብ ግዥው እስከ 45% ድረስ ሊጨመር እንደሚችል አስረድተዋል፡፡ በመሆኑም በጨረታ ቁጥር 13/2014/15 በልዩ ሁኔታ እንዲገዛ ከተጠየቀው 350 ዲክሰን ሼልፍ እና 4 ባለ ሁለት መሣቢያ ፋይል ካቢኔት በስተቀር ሌሎቹ ተጨማሪ ግዥዎች በመመሪያው መሰረት የተገዙ መሆናቸውን፣

በቀረበላቸው ነባራዊ ሁኔታ በሰጡት ምላሽ ላይ ገልጸዋል፡፡

25. የባንኩ የሥራ ኃላፊዎች ከላይ የተጠቀሰውን መልስ ቢሰጡም፡-

- የጨረታ ቁጥር 09/2015/16 በተመለከተ ባንኩና አሸናፊው ድርጅት ውል ተፈራርመው የነበረ በመሆኑ እና ጨረታ ከመውጣቱ በፊት ተገቢው ማጣራት አለመደረጉን እና በዕቅድ አለመመራቱን የሚያሳይ እንዲሁም ከጊዜና ከገንዘብ ጋር በተያያዘ ብክነት በማስከተሉ፣
- የግዥ ጥናቱ ሲከናወን የአፈፃፀም ክፍተቶችንም ለይቶ ለግዥ አፈፃፀሙ ችግር እንዳይሆኑ እና የታቀደው እቅድ ተግባራዊ ሳይሆን እንዳይቀር ማድረግ የሚገባው በመሆኑ፣

- በጨረታ ቁጥሮች 16/2014/15 እና 13/2014/15 በተገዙ ዕቃዎች ላይ የ25% ጭማሪ መከናወን የሚችለው ከአንድ አቅራቢ ለተከናወነ የግዥ ዘዴ መሆኑን በግዥ መመሪያው አንቀፅ 24 ላይ የተጠቀሰ በመሆኑ፣ በኦዲት ነባራዊ ሁኔታው ላይ ግኝት የታየባቸው የጨረታ ሰነዶች ደግሞ በግልፅ ጨረታ የተከናወኑ በመሆናቸው እና ውሉም መጨመር ያለበት 20% ብቻ መሆኑን ስለሚገልፅ
- በጨረታ ቁጥር 13/2014/15 20% እና 25% ጭማሪ ተብሎ ከተጨመረው ሌላ በአስቸኳይ ያስፈልጋል በሚል 350 የዲክሰን ሼልፍ እንዲሁም 4 ባለ 2 መሣቢያ ፋይል ካቢኔት በልዩ ሁኔታ እንዲገዙ የተፈቀዱ መሆናቸውን በተመለከተ አንድ ጨረታ ወጥቶ ዕቃ አሸናፊው ድርጅት እንዲያቀርብ ከተደረገ በኋላ መመሪያ በሚፈቅደው መሰረት ተጨማሪ ግዥ ማድረግ እየተቻለ በልዩ ትዕዛዝ ነው በሚል ግዥ መፈጸሙ ከመመሪያው ውጪ በመሆኑ፣
- የባንኩ የግዥ መመሪያ ከአንድ አቅራቢ ለተከናወነ ግዥ መጨመር ወይም መቀነስ ያለበትን 25% እና በግልፅ ጨረታ ለተከናወነ ግዥ 20% በመጨመር ወይም በመቀነስ መፈጸም እንደሚቻል በመመሪያው ላይ የተቀመጠውን በመተላለፍ በግልፅ ጨረታ ለተከናወነ ግዥ 45% ጭማሪ ማድረግ ይቻላል የሚለው አካሄድ ከመመሪያው ውጪ የሆነ አሰራር በመሆኑ

የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

26. ባንኩ የግዥ ስትራቴጅክ ዕቅድ ወቅታዊ አለመደረጉ፣ ዓመታዊ የግዥ ዕቅዱ በጥናት፣ በፍላጎት ላይ ተመስርቶ እና ከክምችት ያለውን ንብረት ከግምት ውስጥ ሳያስገባ ዕቅድ መዘጋጀቱ፣ በዕቅዱ መሰረት የሚፈለጉ ግዥዎች በወቅቱ እንዳይፈጸሙ እንዲሁም በአንድ ግዥ መገዛት የሚችሉ ዕቃዎች እንዳይገዙ ከማድረጉም በላይ ተጨማሪ እቃዎች ይፈልጋሉ በሚል ሰበብ ከመመሪያው ውጪ ግዥዎችን እንዲፈጸሙ ማድረግ አሰራሮቹ ለሙስና በር እንዲከፈት ያደርጋል፡፡

የግዥ ቴክኒካል ፍላጎት መግለጫ በባለሙያ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፤

27. ባንኩ ለሚገዛቸው ለእያንዳንዱ ግዥዎች የግዥ ቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ (Procurement Specification) በባለሙያ ሊዘጋጅና ተግባራዊ ሊደርግ ይገባል፡፡ ባንኩ ክፍያ ከመፈፀሙ እና ሙሉ ርክክብ ከማካሄዱ በፊት ዕቃዎችን

(የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ) እና ተያያዥ አገልግሎቶችን በባለሙያ በምርምራና በሙከራ ሊያረጋጥ ይገባል፡፡

28. ይሁን እንጂ በባንኩ የሚገዙት እያንዳንዱ ግዥዎች የግዥ ቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ (Procurement Specification) በተገቢው ባለሙያ እንደማይዘጋጁ እና ባንኩ ክፍያ ከመፈፀሙ እና ሙሉ ርክክብ ከማካሄዱ በፊት ዕቃዎችን (የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ) እና ተያያዥ አገልግሎቶችን በባለሙያ በምርምራና በሙከራ እንደማይረጋገጡ በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

29. በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው ከታዩት የባንኩ ዲስትሪክቶች እና ቅርንጫፎች

- ባንኩ በየዓመቱ በከፍተኛ ገንዘብ የሚገዛቸው እቃዎች ከፍተኛ የጥራት ችግር ያለባቸው እና እንደተገዙ አገልግሎት ሳይሰጡ የሚበላሹ መሆናቸው ለምሳሌ የብር መቁጠሪያ ማሽኖች፣ ፎቶ ኮፒ ማሽኖች እና ፕሪንተሮች፣ የኤቲኤም (ATM) ማሽኖች፣ ደንበኞች የሚቀመጡባቸው ወንበሮች፣ ፋይል ካቢኔቶች፣ የሀሳብ መስጫ ሳጥን (ሰጀክሽን ቦክሶች)፣ ወንበሮች፣ ጠረጴዛዎች፣ ፈርኒቸሮች እና ፊክስቸሮች እንዲሁም የውጭ ምንዛሪ መለያ ማሽኖች የመሳሰሉት መኖራቸውን፣
- መለዋወጫቸው ገበያ ላይ የማይገኝ በመሆኑ ዕቃዎቹ ተበላሽተው የተቀመጡበት ሁኔታ መኖሩን እና ዕቃው በመበላሸቱ በስራ ላይ ተፅዕኖ እያመጣ መሆኑን፣ (ለመጥቀስ ሳምሰንግ ፕሪንተሮች እና ዳያቦልድ (Diabold) የተባሉ የኤቲኤም (ATM) ማሽኖች እንዲሁም ሙራቴክ የተባለ ፎቶ ኮፒ ማሽን አልታ በሚባል አቅራቢ የቀረበ)

ምስል 1፡- በጥራት ችግር በስራ ላይ እያሉ ከጥቅም ውጪ የሆኑ ንብረቶችን

- የሚከናወኑ ግዥዎች በባንኩ የግዥ አፈፃፀም መመሪያ አንቀፅ 6 ንዑስ አንቀፅ 6.6 መሰረት አድርጎ ባለመከናወኑ ከውጪ ውበትን የተላበሱ ግን ጥራት የሌላቸው ዕቃዎች እየተገዙና ከጥቅም ውጪ እየሆኑ የሚቀመጡ መሆናቸውን በባንኩ የውስጥ ኦዲት ሪፖርት ላይ መገለፁ፣
- የግዥ ቴክኒክ ፍላጎት መግለጫን (ስፔስፊኬሽንን) የሚመለከተው ባለሙያ ሊያዘጋጀው እንደሚገባና ሲዘጋጅም የንግድ ምልክት (ብራንድ) ሊጠቀስ እንደማይገባ በባንኩ የግዥ መመሪያ አንቀፅ 27.2 ላይ የሚያስገነዝብ ቢሆንም ጨረታ ቁጥር 03/2015/16 የፋክስ ማሽን ብር 1,183,988.52፣ የጨረታ ቁጥሮች 42/2013/14 ብር 2,813,039.15፣ 03/2013/14 ብር 76,143,318.94፣ 64/2013/14 ብር 325,128፣ 01/2014/15 ብር 48,085,087.05፣ 17/2014/15 ብር 16,782,823.60፣ 39/2014/15 ብር 1,009,600.00፣ 20/2014/15 ብር 15,923,715.00፣ 26/2014/15 ብር 13,579,551.04፣ 04/2014/15 ብር 17,044,170.00፣ 25/2014/15 ብር 27,299,517.04፣ 03/2014/15 ብር 10,806,180.00፣ 07/2015/16 ብር 39,335,987.00፣ እና 22/2015/16 ብር 13,448,298.50 የተለያዩ የአይቲ ዕቃዎች በድምሩ ብር 283,780,403.84 ግዥ ቴክኒካል ስፔስፊኬሽኖቹ የአምራቾች መለያ የንግድ ስም (ብራንድ) ጠቅሰው የተገዙ መሆኑን በናሙና ተመርጠው ከታዩ የጨረታ ሰነዶችን በመከለስ ለማወቅ ተችሏል፡፡
- በኦዲቱ ወቅት በናሙና ከታዩት ዋጋቸው በድምሩ ብር 217,304,075.49 የሚያወጡ 14 ግዥዎች (በተለይም የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ዕቃዎች) ክፍያ ከመፈፀሙ እና ሙሉ ርክክብ ከማድረጉ በፊት ዕቃዎቹ በቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ (ስፔስፊኬሽን) መሰረት ስለመሆናቸው በተገቢው ባለሙያ ስለመረጋገጡ የሚያስረዳ ማስረጃ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ አልቀረበም፡፡ (ዝርዝሩ በአባሪ 5 ተያይዟል፡፡)

30. ስለሁኔታው የባንኩ ኃላፊዎች ተጠይቀው፡-

- የጠቀሜታ መስፈርት ዝግጅትን የተሻለ ጥራት ያላቸውን ዕቃዎች ብቻ በሚለይ መልኩ የመመዘኛ መስፈርቶቹን በየጊዜው በማሻሻል ላይ እንደሚገኙ፣

- የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ ዝግጅት ላይ በባንኩ የግዥ መመሪያ አንቀፅ 27.2.5 መሰረት የተከናወኑ የጠቀሜታ መዘርዝሮች እንደሆኑና በእያንዳንዳቸው ዕቃዎች ግዥ ላይ "...or equivalent" የሚል ቃል አብሮ የተገለፀ መሆኑን
- በግዥ መመሪያው አንቀፅ 38.3 መሰረት በጠቀሜታ መስፈርቱ መሰረት አቅራቢው ዕቃውን ያስገባ ስለመሆኑ እና በዕቃ መረከቢያ ሰነድ (MRN) ላይ ፍተሻው በተሳካ ሁኔታ መከናወኑን ለማረጋገጥ ፍተሻውን ያካሄደው ባለሙያ ስምና ፊርማ በሚያዘው ቦታ ላይ ስምና ፊርማውን የሚያቀምጥ መሆኑን

በቀረበላቸው ነባራዊ ሁኔታ በሰጡት ምላሽ ላይ ገልጸዋል፡፡

31. የባንኩ ሀላፊዎች ይንን ቢሉም፡-

- የንግድ ምልክት (ብራንድ) የተጠቀሰባቸው ዕቃዎች በአብዛኛው የአይቲ ዕቃዎች በመሆናቸው እነዚህን ዕቃዎች በመመሪያው አንቀፅ 27.2.5 ላይ በተጠቀሰው መሰረት ፍላጎትን በትክክል ሊገልፅ የሚችል መግለጫ ማዘጋጀት አስቸጋሪ የሚሆንበት ሁኔታ ስለማይኖር ብራንድ (የንግድ ምልክት) ሙሉ በሙሉ ማለት በሚያስችል መልኩ የተጠቀሰ በመሆኑ
- በኦዲት ግኝቱ ወቅት ለተዘረዘሩት የጨረታ ሰነዶች እና ንብረቶቹ በስፔሲፊኬሽኑ መሰረት መሆናቸው ተረጋግጠው ርክክብ የተፈጸመባቸው ሰነዶች በተሟላ ሁኔታ ማስረጃው ያልቀረበና ያልተያያዘ በመሆኑ

የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

32. የግዥ ቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ (Procurement Specification) በተገቢው ባለሙያ ባለመዘጋጀቱ እንዲሁም ባንኩ ክፍያ ከመፈፀሙ እና ሙሉ ርክክብ ከማካሄዱ በፊት ዕቃዎችን (የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ) እና ተያያዥ አገልግሎቶችን በባለሙያ በምርምራና በሙከራ ባለመረጋገጡ ጉልህ የሆነ የጥራት ችግር ያለባቸው እንዲሁም ተገዝተው ምንም አገልግሎት ሳይሰጡ የሚበላሹ በርካታ ንብረቶች እንደሚገዙ ከማድረጉም በላይ የንግድ ምልክቶችን እየጠቀሱ ጨረታ ማውጣት ባንኩን ለሙስና እና ለብልሹ አሰራር ተጋላጭ ያደርገዋል፡፡

ጨረታዎች በተያዘላቸው ጊዜ የሚጠናቀቁ መሆናቸውን በተመለከተ፤

33. ጨረታዎች ተዘጋጅተው ሙሉ ሂደታቸውን ጨርሰው አሸናፊው ድርጅት እንዲያውቅ ተደርጎ ግዥው በተያዘው የጊዜ ውስጥ መከናወን ይኖርበታል፡፡

34. ነገር ግን በኦዲቱ ወቅት በናሙና ከታዩ ባንኩ ካወጣቸው ጨረታዎች መካከል የሚዘጋጁት የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫዎች በየጊዜው በሚካሄድ የገበያ ጥናቶች በመመርኮዝ እና አዳዲስ ፍላጎቶችና የቴክኖሎጂ ለውጦች ግምት ውስጥ በማስገባት ስለማይከለስ የባንኩ በርካታ ግዥዎች የሚቋረጡ እና የሚዘገዩበት መሆኑ ለአብነት፡-

- ጨረታ ቁጥር 22/2015/16 እ.አ.አ በየካቲት 17/2016 ሁለት ዕቃዎችን ለመግዛት ጋዜጣ የወጣ ቢሆንም ምክንያቱ ባልተገለፀ ሁኔታ አንደኛው ዕቃ ሳይገዛ መቅረቱ፣
- ከሶስት የጨረታ ቁጥሮች ማለትም ከ13/2012/13 አቅራቢው ውል ተዋውሎ ዕቃውን ባለማቅረቡ፣ ከ42/2013/14 ብቁ ተጫራቾች ባለመገኘታቸው እና ከ23/2013/14 የተጋነነ ዋጋ በመቅረቡ በሚሉ ምክንያቶች ሊገዙ የነበሩ 7 የሚሆኑ ዕቃዎች ተጠቃለው በ64/2013/14 ላይ በድጋሚ እንዲወጡ ቢደረግም ከሰባቱ ዕቃዎች ውስጥ የአምስቱ ዕቃዎች ግዥ ምክንያቱ ባልታወቀ ሁኔታ የተቋረጠና በውስን ጨረታ እንዲገዙ ለውሳኔ የቀረቡ መሆኑ ይህም አራት ወራትን የፈጀ መሆኑ፣
- የጨረታ ቁጥር 25/2014/15 የማስታወቂያ ጋዜጣው እ.አ.አ በጥቅምት 3/2014 የወጣ ሲሆን ስፔስፊኬሽኑ መስተካከል በማስፈለጉ እ.አ.አ በሚያዝያ 30/2015 ወደ ሌላ ጨረታ እንዲዞር የተደረገ መሆኑ፣
- 04/2014/15 ማስታወቂያ የወጣበት ጋዜጣ ያልተያያዘና ምክንያቱ በግልፅ ባልታወቀበት ሁኔታ ሊገዙ ከታሰቡት ሁለት ዕቃዎች አንደኛው እንዲሰረዝ የተደረገ ሲሆን ለዚህም አራት ወራት የፈጀ መሆኑ፣
- 33/2015/16 የጀነሬተር ግዥ ሲሆን ማስታወቂያው በየካቲት 20/2008 የወጣና ሙሉ በሙሉ የተሰረዘ እና 39 ቀናት የፈጀ መሆኑ፣
- የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ (ስፔስፊኬሽን) በአንድ ጨረታ ሂደት ላይ ከሁለት ጊዜ በላይ እንደሚሻሻል እና ጨረታ ወጥቶ ስፔስፊኬሽን ከተሰጠ በኋላ ለተጫራቾች የስፔስፊኬሽን ማስተካከያ ተብሎ ደብዳቤ በተደጋጋሚ የሚፃፍላቸው መሆኑ፣

በኦዲት ወቅት ከተሰበሰበው መረጃ እና በናሙና ተመርጠው ከታዩት የባንኩ ዲስትሪክት እና ቅርንጫፍ ስራ አስኪያጆች በቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

35. ስለሁኔታው የባንኩ ኃላፊዎች ተጠይቀው የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫዎች ዝግጅት ለማጠናከርና ከአቅም ውስንነት ጋር የሚያጋጥሙ ክፍተቶችን ለመዝጋት ስራው በክፍል ደረጃ እንዲዋቀርና በየግዥ ዘርፉ ለሚያስፈልጉ ክፍተቶች በባለሙያዎች እንዲደራጅ የተደረገ ሲሆን የካቲት 30/2008 ዓ/ም ጀምሮ ተግባራዊ መሆኑን በነባራዊ ሁኔታ በሰጡት መልስ ላይ ገልፀዋል፡፡

36. በፍላጎት ላይ እና በበቂ ጥናት ላይ ተመስርቶ ጨረታዎች የማይወጡ ከሆነ ግዥዎች በተደጋጋሚ የሚቋረጡ በመሆናቸው የግዥ ሂደቱ ኢኮኖሚያዊ እንዳይሆንና ባንኩን ለተለያዩ አግባብነት የሌላቸው ወጪዎች እንዲዳረግ ከማድረጉም በላይ ከሚገዙት ንብረቶች ሊገኝ የነበረውን ጥቅም እንዲጓተት ያደርጋል፡፡

የግዥ ቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ የሚያዘጋጅውና የሚገመግመው ባለሙያን በተመለከተ፤

37. ባንኩ ለሚገዛቸው ለእያንዳንዱ ግዥዎች የግዥ ቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ (Procurement Specification) የሚያዘጋጅ እና የቴክኒክ ግምገማ (Evalution) የሚያደርግ ባለሙያ እንዲለያይ ሊያደርግ ይገባል፡፡

38. በኦዲት ወቅት ባንኩ ለሚገዛቸው ግዥዎች የግዥ ቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ (Procurement Specification) የሚያዘጋጅ እና የቴክኒክ ግምገማ (Evalution) የሚያደርግ ባለሙያ እንዲለያይ ያልተደረገበት ሁኔታ መኖሩን ከተከለሰው የግዥ ሰነዶች ለማወቅ ተችሏል፡፡

39. ስለሁኔታው የባንኩ ኃላፊዎች ተጠይቀው የጠቀሜታ ዝርዝር የሚያዘጋጁና የሚገመግሙ ባለሙያዎች በክፍል ደረጃ ተለይተው እንደተዋቀሩ እና ከዚህ ቀደም የግዥ ክፍሉ የባለሙያ እጥረት የነበረበት በመሆኑ ከዚህ በፊት በነበሩት የጨረታ ሰነዶች አልፎ አልፎ የጨረታ ሰነዶች ባዘጋጁት ባለሙያዎች ጨረታዎች የሚገመገሙበት አጋጣሚዎች እንደነበሩ በቀረበላቸው ነባራዊ ሁኔታ በሰጡት ምላሽ ላይ ገልፀዋል፡፡

40. ግዥዎች የግዥ ቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ (Procurement Specification) የሚያዘጋጅ እና የቴክኒክ ግምገማ (Evalution) የሚያደርግ ባለሙያ በመመሪያው መሰረት ባለመለየቱ የጥቅም ግጭት እንዲያስከትል በር በመክፍት ለብልሹ አሰራር እና ለሙስና ተጋላጭ ሊያደርግ እንዲሁም ጥራት የሌላቸው ዕቃዎች እንዲገዙ ሊያደርግ ይችላል፡፡

ግዥዎች በመመሪያው መሰረት በውድድር መፈጸማቸውን በተመለከተ፤

41. ባንኩ ለሚፈፅማቸው ግዥዎች በግዥ መመሪያው መሰረት በውድድር ሊያከናውን ይገባል፡፡

42. ይሁን እንጂ የባንኩ አንዳንድ ግዥዎች በመመሪያው ላይ በተቀመጠው መስፈርት መሰረት በውድድር መከናወን ሲገባቸው እንደማይከናወኑ እና ያለውድድር የሚፈጸሙ ግዥዎች እንዳሉ በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

43. በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው ከታዩት የግዥ ሰነዶች ውስጥ፣

ሀ. የባንኩ የሕዳሴ ህንጻ ግንባታን በተመለከተ

44. ንግድ ባንኩ አዲስ አበባ መገናኛ አካባቢ ህዳሴ ህንፃ ብሎ ለሰየመው ባለ ሰባት ፎቅ (G+7) ህንጻ ለመገንባት ጨረታ አውጥቶ ከአሸናፊው ድርጅት ተክለ ብርሀን አምባዬ ኮንስትራክሽን ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ጋር በብር 100,745,043.04 ውል ተዋውሎ ነበር፡፡

45. ነገር ግን በተጨማሪነት ለሚታዘዘው የግንባታ ስራ ከዋናው ውል ጠቅላላ ዋጋ 30% መብለጥ እንደሌለበት የባንኩ ግዥ መመሪያ አንቀፅ 24.1.2(ለ) የተገለጸ ቢሆንም ከውሉ በኋላ ባንኩ የህንጻውን ከፍታ ከ7 ፎቅ ወደ 12 ፎቅ ለማሳደግ ለተጨማሪ አምስት ወላል ግንባታ ማለትም ከ8ኛ እስከ 12ኛ ፎቅ በብር 24,723,036.94 (የውሉ 24.5%) እንዲሁም ህንጻውን ለስልጠና ማዕከልነት ለመገልገል እንዲያስችል ተብሎ ሌላ ተጨማሪ ግንባታ በብር 52,896,654.15 (የውሉ 52.5%) በድምሩ ብር 77,619,691.09 የመጀመሪያው ውል (77.0%) ጨረታ ሳይወጣ (ያለውድድር) በቀጥታ የመጀመሪያውን ጨረታ ከአሸነፈው ኮንትራክተር ተክለ ብርሀን አምባዬ ኮንስትራክሽን ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ጋር ሁለት ተጨማሪ ውሎች (Supplementary agreements) የተፈራረመ መሆኑ ታውቋል፡፡

46. ስለጉዳዩ የባንኩ የሥራ ኃላፊዎች ተጠይቀው የመገናኛ ህንጻ ፕሮጀክት (ህዳሴ ህንፃ) ከከተማው አስተዳደር የህንፃ ቁመት ጋር በማጣጣም G+7 ለመገንባት የታቀደ እንደነበር በኋላ ግን የአካባቢው የህንፃ ቁመት ህግ በመሻሻሉ ጥናት ተካሂዶ በማፀደቅ ህንፃው ወደ G+12 እንዲያድግ የተወሰና ለዚህም ተጨማሪ ውል (Supplementary Contract) እንደተዋዋለና ይህም ተጨማሪ ውል ከመጀመሪያው ውል ዋጋ ከ30% በታች እንደሆነ፣ የሰው ሀይል ለማሰልጠን የተዘጋጀ ቦታ ባለመኖሩ ህንፃውን በአስቸኳይ ከቢሮ አገልግሎት ወደ የልህቀት ማዕከል (Center of Excellence) ለመቀየር በባንኩ በመወሰኑ ተቀፅላ ውል 2 (Supplementary Contract) እንደተደረገና ይህ ስራ ከዋናው የህንፃ ግንባታ ጋር የተያያዘ እና ሊለያይ የማይችል በመሆኑ ለዚሁ ተቋራጭ መሰጠቱን በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ፣ ለረቂቅ ሪፖርቱ በጽሁፍ በሰጡት ምላሽ ላይ እና በመውጫ ስብሰባ ወቅት ገልጸዋል፡፡

47. ኃላፊዎቹ ይህን ይበሉ እንጂ

- የህንጻውን ከፍታ ከ7 ፎቅ ወደ 12 ፎቅ ለማሳደግ የተደረገውን የብር 24,723,036.94 (የውሉ 24.5%) ተጨማሪ ውል መለየት ያስቸግር ነበር ቢባል እንኳን ህንፃውን ለሥልጠና ማዕከል ለማዋል የተደረገውን የብር 52,896,654.15 በጨረታ አወዳድሮ መስጠት የሚቻል በመሆኑና አስቀድሞም የባንኩን ራዕይ ታሳቢ በማድረግ ማቀድ የሚቻል በመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ አልተቀበልንም፡፤

ለ. ፈርኒቸር ፊክስቸር እና የኪችን ዕቃዎች ግዥን በተመለከተ

48. ንግድ ባንኩ ያለውድድር (ጨረታ ሳያከናወን)

- አዲስ አበባ መገናኛ አካባቢ ህዳሴ ህንፃ ብሎ ለሰየመው ህንጻ አገልግሎት የሚውል ለስልጠና የሚሆኑ ፈርኒቸር ፊክስቸር ((Furniture and Fixtures)፣ የኪችን እና የፓርቲሽን ዕቃዎች እ.አ.አ. በነሀሴ 25/2014 በብር 123,341,888.89፣
- ለባንኩ ጳዉሎስ ቅርንጫፍ ህንጻ የሚያገለግሉ ፈርኒቸሮች፣ ፊክስቸሮች (Furniture and Fixtures)፣ የኪችን እና የፓርቲሽን እቃዎች በቀን እ.ኤ.አ መስከረም 29/2015 በብር 66,865,116.91

በድምሩ ብር 190,207,005.8 የሚያወጣ ግዥ ከግዢ መመሪያ ውጭ ከተክለ ብርሀን አምባዬ ኮንስትራክሽን ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር በፕሮሰስ ካውንስሉ (የባንኩ ሥራ አመራር) ውሳኔ በቀጥታ ግዥ እንዲፈጽም የተደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡

49. ስለጉዳዩ የባንኩ ኃላፊዎች ተጠይቀው በጳውሎስ ቅርንጫፍ ላይ በመገናኛ ህንፃ ላይ የታየውን የፈርኒቸር፣ የፊክስቸር እና የኪችን ዕቃዎች በአስቸኳይ ለመግዛት እና እቃዎቹ ጥራት እና ቀጣይነት ያላቸው እንዲሆኑ በማስፈለጉ መልካም የስራ አፈፃፀም መሰረት በማድረግ የባንኩ ፕሮሰስ ካውንስል በወሰነው እና በግዥ መመሪያው አንቀፅ 24.1.7 መሰረት በተፈቀደው አካሄድ በቀጥታ ግዥ ከተክለ ብርሀን አምባዬ ኮንስትራክሽን ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር (Contract for Furniture, Fixture and Equipment) እንደተፈረመ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ፣ ለረቂቅ ሪፖርቱ በጽሁፍ በሰጡት ምላሽ ላይ እና በመውጫ ስብሰባ ወቅት ገልጸዋል፡፡

50. ኃላፊዎቹ ይህን ይበሉ እንጂ ዕቃዎቹን በዕቅድና የባንኩን የግዥ መመሪያ የሚቻልና በአስቸኳይ ለመግዛት የሚያስገድድ ምንም አይነት አሳማኝ ምክንያት የሌለ በመሆኑና ግዥውን የወሰነው የባንኩ ፕሮሰስ ካውንስልም ቢሆን በግዥ መመሪያው መሰረት ግዥን የማጽደቅ ስልጣን ስለሌለው የተሰጠውን ምላሽ አልተቀበልነውም፡፡

ሐ. የጳውሎስ ቅርንጫፍ ሕንጻ ግንባታ በተመለከተ

51. የባንኩ ጳዉሎስ ቅርንጫፍ ህንፃ ሳትኮን የሚባል ተቋራጭ ስራውን ጨረታውን አሸንፎ ግንባታ ከጀመረ በኋላ በውሉ መሰረት ሥራውን ባለመሥራቱ የባንኩ ፕሮሰስ ካውንስል ውሉ እንዲቋረጥ ወስኖ ቀሪ የግንባታ ሥራዎችን እንዲያጠናቅቅ ብር 39,885,624.25 እ.አ.አ በነሀሴ 17 ቀን 2015 ለተክለብርሃን አምባዬ ኮንስትራክሽን ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ያለጨረታ በቀጥታ ከመመሪያ ውጭ በባንኩ ፕሮሰስ ካዉንስል ውሳኔ መሰረት እንዲከናውን የተደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡

52. ስለጉዳዩ የባንኩ ኃላፊዎች ተጠይቀው ባንኩ የጳውሎስ ቅርንጫፍ ህንፃ ግንባታ ፕሮጀክትን በጨረታ ሳትኮን ለሚባል ተቋራጭ የሰጠና ይህ ተቋራጭ ስራውን ሳያጠናቅቅ በመቅረቱ በፕሮሰስ ካውንስሉ ውሳኔ መሰረት ስራው እንዲቋረጥ የተደረገ ሲሆን የቀሩ ስራዎችን ለማጠናቀቅና ህንፃውን ለማሳደግ በመፈለጉ የጨረታ ሂደት ሳይጠበቅ በአስቸኳይ ለመፈፀም በባንኩ ፕሮሰስ ካውንስል እ.አ.አ ኦገስት 17/2015 በተደረገው ጉባኤ ግዥው በቀጥታ ለተክለብርሃን አምባዬ እንደተሰጠ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ፣ ለረቂቅ ሪፖርቱ በጽሁፍ በሰጡት ምላሽ ላይ እና በመውጫ ስብሰባ ወቅት ገልጸዋል፡፡

53. ኃላፊዎቹ ይህን ይበሉ እንጂ ቀሪውን ግንባታ ያለጨረታ ለሌላ የሥራ ተቋራጭ ለመሰጠት የሚያስገድድ ምንም አይነት አሳማኝ ምክንያት የሌለና ከዚህ ተቋራጭ

በተደጋጋሚ የባንኩን የግዢ መመሪያ ባልተከተለ መንገድ ሲገባ የነበረውን ውል በጳውሎስ ቅርንጫፍም ላይ በመድገም ቀሪውን ግንባታ በቀጥታ ለሥራ ተቋራጩ እንዲሰጥ የወሰነው የባንኩ ፕሮሰስ ካውንስል በግዥ መመሪያው መሰረት ግዥን የማጽደቅ ስልጣን ስለሌለው የተሰጠውን ምላሽ አልተቀበልነውም፡፡

መ. በውስን ጨረታ የተከናወኑ ግዥዎችን በተመለከተ፣

54. በውስን ጨረታ የሚከናወኑ ግዥዎች በግዥ መመሪያው አንቀፅ 22.1.2 አቅራቢዎቹ የተወሰኑ ብቻ መሆናቸው ሲረጋገጥ ወይንም በአንቀፅ 22.2.2 እንደተጠቀሰው የገንዘብ መጠናቸው ከብር 750,000.00 መብለጥ የሌለበት ቢሆንም በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩ የግዥ ሰነዶች አቅራቢዎቹ የተወሰኑ መሆናቸው ሳይረጋገጥ እንዲሁም የገንዘብ መጠናቸው ከብር 750,000 የበለጠ ግዥዎች በውስን ጨረታ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡ ዝርዝሩ በሚከተለው ሰንጠረዥ ተመልክቷል፡፡

በጨረታ ቁጥር	የድርጅቱ ስም	የተገዛው ዕቃ	የገንዘቡ መጠን
64/2014/15	ከኤንሲአር ኖርዝ አፍሪካ ሊሚትድ	የኤትኤም ማሽን	3,100,040.00 USD
06/2015/16	ከኤንሲአር ኖርዝ አፍሪካ ሊሚትድ	የኤትኤም ማሽን	2,430,040.00 USD
01/2014/15	ከስናፕ ትሬዲንግ ኤንድ ኢንደስትሪ ሊሚትድ እና ከአልታ ኮምፒውቴክ	የአይቲ ዕቃዎች	ብር 48,085,087.05
44/2015/16	ከአይሲቲ ወርልድ ዋይድ ሊሚትድ	የፔይመንት ስዊች	ብር 4,171,240.00

ሰንጠረዥ 3፡- ያለበቂ ምክንያት በውስን ጨረታ የተገዙ የግዥ ሰነዶች

በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

55. ስለሁኔታው የባንኩ ኃላፊዎች ተጠይቀው፡-

- የጨረታ ቁጥር 64/2014/15 እና 06/2015/16 የኤቲኤም ግዥዎችን በተመለከተ በመመሪያው አንቀፅ 22.1.2 መሰረት በአለም አቀፍ ውስን ጨረታ የግዥ ዘዴ የተከናወነ መሆኑን

- የጨረታ ቁጥር 01/2014/15 የኮምፒውተሮች ግዥን በተመለከተ አዲስ ለሚከፈቱ ቅርንጫፎች አስቸኳይነታቸው ከግምት ውስጥ ገብቶ በመመሪያው አንቀፅ 22.1.4 መሰረት በአቅራቢነት ከተመዘገቡት አቅራቢዎች በብሄራዊ ውስን ጨረታ ሂደት ግዥ የተከናወነ መሆኑን፣
- ጨረታ ቁጥር 44/2015/16 ካርድ ፔይመንት ስዊች ሶፍትዌርና አገልግሎት ግዥን በተመለከተ በግዥ መመሪያው አንቀፅ 22.1.2 መሰረት በዓለም ታዋቂ የሆኑ ዓለም አቀፍ የሶፍትዌር እና አገልግሎት አቅራቢዎችን ዝርዝር ለፕሬዝዳንቱ አቅርቦ በማስፀደቅ በዓለም አቀፍ ውስን ጨረታ ግዥ የተከናወነ መሆኑን በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ፣ ለረቂቅ ሪፖርቱ በጽሁፍ በሰጡት ምላሽ ላይ እና በመውጫ ስብሰባ ወቅት ገልጸዋል፡፡

56. ኃላፊዎቹ ይህንን ቢሉም፡-

  - በጨረታ ቁጥሮች 64/2014/15 እና 06/2015/16 የኤቲኤም ግዥዎችን በተመለከተ አቅራቢዎች ውስን የሚሆኑበት ሁኔታ ባለመኖሩ ካለ ደግሞ እነዚህ አቅራቢዎች ውስን ስለመሆናቸው መረጃ ባለመቅረቡ እና ግዥው ከመመሪያ ውጭ በውስን ጨረታ እንዲከናወን የተፈቀደበት ማስረጃ ባለመቅረቡ፣
  - በጨረታ ቁጥር 01/2014/15 የኮምፒውተሮች ግዥን በተመለከተ በአመት ውስጥ አዲስ የሚከፈቱ ቅርንጫፎች የሚታወቁና ለቅርንጫፎቹ የሚገዙ ዕቃዎች በዕቅድ የሚያዙ በመሆናቸው አስቸኳይ ተብለው የሚገዙበት ምክንያት ግልፅ ባለመሆኑና የማያስኬድ አሰራር በመሆኑ የኮምፒዩተሮቹም ግዥ ባንኩ በስትራቴጂክ ዕቅድ እና በግዥ ዕቅድ እንመራለን ከሚለው ሃሳብ ጋር የሚቃረን በመሆኑ፣
  - ጨረታ ቁጥር 44/2015/16 ካርድ ፔይመንት ስዊች ሶፍትዌርና አገልግሎት ግዥን ለማከናወን አሸናፊ የሆነው ከአይሲቲ ወርልድ ዋይድ ሊሚትድ ተዘርዝረው ከቀረቡት ድርጅቶች ዝርዝር ውስጥ ስለሌለ ወይንም የየትኛው ወኪል እንደሆነ ማስረጃ ባለመቅረቡ፣

የተሰጠውን ምላሽ አልተቀበልነውም፡፡

ሠ. ያለውድድር የተከናወኑ ግዥዎች፡

57. በጨረታ ቁጥር 06/2015/16 ለተገዙት 400 የATM ማሽኖችን ከሞጆ ወደብ ወደ አዲስ አበባ ለማጓጓዝ ሞቲ ኢንጅነሪንግ ለተባለ ድርጅት ያለ ውድድር በብር 258,971.43 የአገልግሎት ግዥ ተከናውኗል፡፡

58. ስለጉዳዩ የባንኩ ኃላፊዎች ተጠይቀው የጨረታ ቁጥር 06/2015/16 የተገዙት የኤቲኤም ማሽኖች ከሞጆ ደረቅ ወደብ ወደ ባንኩ ያጓጉዝ የነበረው የኢትዮጵያ ባህር ትራስፖርትና ሎጂስቲክስ አገልግሎት በሌላ ስራ የተሰማራ ስለነበር ባንኩ ለሌላ አገልግሎት ሰጪ ቢሰጥ በድጋሚ ኢንሹራንስ እንዳይከፍል፣ አገልግሎቱን የሚሰጥ ሌላ ድርጅት ለማወዳደር ጊዜ የሚወስድ በመሆኑ፣ በደረቅ ወደቡ ላይ ዕቃው ሲቆይ ከፍተኛ የመጋዘን ኪራይ የሚያስከፍል በመሆኑ እና ሞቲ ኢንጅነሪንግ ከዚህ ቀደም በስራው ላይ ልምድ ያለው በመሆኑ ለማሽኑ ደኅንነት ሲባል የአምራቹ የሀገር ውስጥ ተወካይ የሆነውን ሞቲ ኢንጅነሪንግ የመረጡ መሆኑን፤ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ፣ ለረቂቅ ሪፖርቱ በጽሁፍ በሰጡት ምላሽ ላይ እና በመውጫ ስብሰባ ወቅት ገልጸዋል፡፡

59. ኃላፊዎቹ ይህን ምላሽ ቢሰጡም የኤቲኤም ማሽኖች ሞቲ ኢንጅነሪንግ በተባለ ድርጅት እንዲጓጓዙ መደረጋቸውን በተመለከተ እንደችግር የተነሱት ጉዳዮች ተዘርዝረው ለግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ ቀርበው የግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ ያፀደቀበት ማስረጃ ያልተያያዘና በቂ ልምድ አለው ለተባለውም ማስረጃ ባለመቅረቡ እና ዕቃዎቹ መቼ እንደሚደርሱ ስለሚታወቅ እንዴት እንደሚጓጓዙ አስቀድሞ ማቀድ ይቻል ስለነበረ የተሰጠውን ምላሽ አልተቀበልነውም፡፡

60. ባንኩ ያለጨረታ እንዲሁም ያለበቂ ምክንያት በውስን ጨረታ እቃዎችን እንዲገዙ መደረጉ፣ እንዲሁም ግዥ ማጽደቅ ሥልጣን በሌለው አካል ግዥዎች እንዲጸድቁ መደረጋቸው ግዥዎች ለሙስናና ለብልሹ አሰራር ተጋላጭ እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡

ግዥ የማፅደቅ ስራ የግዥ አፅዳቂ ቡድን የሚከናወን መሆኑን በተለመከተ፤

61. ግዥ የማፅደቅ ስራ በግዥ አፅዳቂ ቡድን ብቻ ሊፈፀም ይገባል፡፡

62. ይሁን እንጂ አንዳንድ የባንኩ የግዥዎች የግዥ አጽዳቂ ቡድን እያሉ በባንኩ ፕሬዝዳንት እንዲጸድቁ እንደሚደረግ በኦዲት ወቅት ከተከለሱት የግዥ ሰነዶች ለማወቅ ተችሏል፡፡ ለአብነት የጨረታ ቁጥር 64/2014/15 400 ኤ.ቲ.ኤም በ3,100,040.00 የአሜሪካን ዶላር በውስን ጨረታ ግዥ ለመፈፀም እ.አ.አ. በቀን 09/02/2015 ለኮሚቴ ቀርቦ ግዥው ቀጥታ የኤ.ቲ.ኤም አምራች የሆኑት ዲቦልድ፣

ኤን.ሲ.አር እና ዊንከር በውድድሩ እንዲሳተፉና ከድርጅቶቹ እንዲገዙ በባንኩ ፕሬዘዳንት እንዲጸድቅ የተደረገ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

63. ስለሁኔታው የባንኩ ኃላፊዎች ተጠይቀው ጨረታ ቁጥር 64/2014/15 ኤቲኤም ለመግዛት ለበጀት አመቱ ወጥቶ የነበረው ጨረታ የተሰረዘ በመሆኑና የበጀት አመቱም የተጋመሰ በመሆኑ የግዥ መመሪያው አንቀፅ 22.1.4 መሰረት ግዥውን ለማፋጠን በግዥ ኮሚቴው የውሳኔ ሀሳብ እ.ኢ.አ 21/02/2015 ቀርቦ በፕሬዝዳንቱ በማስጸደቅ በዓለም ላይ ታዋቂ የሆኑ የኤቲኤም አምራች ድርጅቶችን በመጋበዝ በዓለም አቀፍ ውስን ጨረታ ግዥው ተከናውኗል በማለት በቀረበላቸው ነባራዊ ሁኔታ በሰጡት ምላሽ ላይ ገልፀዋል፡፡

64. ኃላፊዎቹ ይህን ምላሽ ቢሰጡም ጨረታዎች በተደጋጋሚ በመሰረዛቸው ምክንያት ግዥዎች ካሉት የኤቲኤም አቅራቢዎች ውስጥ ሦስቱ ብቻ በውስን ጨረታ እንዲወዳደሩና ሌሎች አምራቾች ወይም አቅራቢዎች ያልተጋበዙበት ምክንያት ባለመቅረቡ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

65. የባንኩ ግዥ በግዥ አፅዳቂ ቡድን መወሰን ሲገባው በባንኩ የበላይ ሃላፊ መወሰኑ በግዥ ሂደቱ ላይ ቅሬታ ቢቀርብ የባንኩ ፕሬዝዳንት የወሰኑትን ውሳኔ መልሰው ቅሬታውን ማስተናገድ በገለልተኝነት ለመመልከት ስለሚያስቸግራቸው እና ለወደፊትም መመሪያውን ለመጣስ በር ይከፍታል፡፡

2.2 የባንኩ ንብረት አስተዳደር ወጪ ቆጣቢ ውጤታማና ቀልጣፋ ስለመሆኑ፤

2.2.1 የንብረት አያያዝ እና አጠቃቀም ስርዓት መኖሩንና ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፤

በባንኩ የሚገዙ ዕቃዎች በወቅቱ ማሰራጨትን በተመለከተ፤

66. በባንኩ የየሥራ ክፍሎቹን፣ ዲስትሪክቶችን ፍላጎት መሰረት አድርጎ ባዘጋጀው የግዥ ዕቅድ መሰረት የተገዙ ዕቃዎች የግዥ ጥያቄ ላቀረበው ክፍል ወይም ቅርንጫፍ በቀጥታ ወይም በዲስትሪክቶቹ በኩል በወቅቱ ሊሰራጩና ሥራ ላይ ሊውሉ ይገባል፡፡

67. ይሁን እንጂ የሚገዙ እቃዎች በወቅቱ ለባንኩ ዲስትሪክቶች እና ቅርንጫፎች እንደማይደርሱ በኦዲት ወቅት ከተከለሰው መረጃ እንዲሁም ከዲስትሪክት እና ከቅርንጫፍ ስራ አስኪያጆች ለማወቅ ተችሏል፡፡ ለአብነት፡-

- እ.እ.እ. በ2015 ከውስጥ ኦዲት ሪፖርት ባንኩ የገዛቸው ዕቃዎች የግዥ ጥያቄ ላቀረበው ዲስትሪክት ወይም ቅርንጫፍ በወቅቱ ሳያሰራጭ ከ8 ወር እስከ 36 ወር (3 ዓመት) ድረስ እንደሚዘገይ በናሙና የታዩ ዲስትሪክቶቹና ቅርንጫፎቹ የተገለፀ መሆኑ፣
- በናሙና ተመርጠው ከታዩት የአዲስ አበባ፣ የሐዋሳ እና የሻሸመኔ ዲስትሪክቶችና ቅርንጫፎች የጠየቁት ዕቃ በወቅቱ እንደማይደርሳቸው በቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ መግለጻቸው፣
- በተለያየ ጊዜ ተገዝተው ለሐዋሳ ዲስትሪክት የተሰራጩ የገንዘብ ማስቀመጫ ሳጥኖች (ካሽ ቦክሶች)፣ መቀመጫ ወንበሮች፣ የመኪና ጎማዎች፣ የአይቲ ዕቃዎች እና ራውተሮች በሀዋሳ ዲስትሪክት መጋዘን ውስጥ የሚገኙ ቢሆንም የመስክ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት የካቲት 6/2009 ዓ/ም (እ.አ.አ የካቲት 13/2017) ድረስ ለቅርንጫፎች ሳይሰራጩ የተቀመጡ መሆኑ፣
- በሻሸመኔ ዲስትሪክት መጋዘን ውስጥ ኢፐሰን እና ሳምሰንግ ፕሪንተሮች፣ ኮምፒውተሮች፣ መለዋወጫዎች፣ ፋክስ ማሽኖች እና ስካነሮች ከአንድ አመት በላይ ለቅርንጫፎች ሳይሰራጩ የመስክ ኦዲቱ እስከተከተጠናቀቀበት የካቲት 9/2009 (እ.አ.አ የካቲት 13/2017) ሳይሰራጩ የተቀመጡ መሆኑ፣

በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

68. ስለሁኔታው የባንኩ ኃላፊዎች ተጠይቀው ሁሉም የዲስትሪክት ፅ/ቤቶች እ.አ.አ በ2009 መተግበር በጀመሩት የባንኩ BPR ከ12-15 ቅርንጫፎችን እንዲያስተዳድሩ የተቋቋሙ ቢሆንም በአሁኑ ወቅት ሁሉም ዲስትሪክቶች በአማካኝ ከ100-150 ቅርንጫፎችን የሚያስተዳድሩ በመሆኑ እና ለነዚህ ሁሉ ቅርንጫፎች ከማዕከል የወሰዱትን ንብረት ለማከፋፈል እያንዳንዳቸው ያላቸው አንድ ከባድ መኪና ነው፡፡ ይህም የዐቅም ውስንነት ችግር እንዲኖር ያደረገና ይህንንም ችግር ለመፍታት ለዲስትሪክቶች ተጨማሪ መኪናዎች ግዥ በባለፉት ሁለት አመታት እየተፈጸመ እንደሚገኝ በቀረበላቸው ነባራዊ ሁኔታ በሰጡት ምላሽ ላይ ገልፀዋል፡፡

69. ኃላፊዎቹ ይህን ይበሉ እንጂ ዕቃዎቹ ለባንኩ አገልግሎት ከሚሰጡት ጠቀሜታ አንጻር የትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡ ድርጅቶችን በመጠቀም ማዳረስ ይቻል ስለነበር የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

70. የተገዙ ዕቃዎች ለዲስትሪክቶች እና ለቅርንጫፎች በወቅቱ አለማሰራጨቱ ባንኩ ቀልጣፋ አገልግሎቱን ተደራሽ ለማድረግ እንቅፋት ሊሆን ከመቻሉም በላይ ንብረቶቹ ሥራ ላይ ሳይውሉ ሊበላሹ የሚችሉበት ሁኔታ ይፈጥራል፡፡

የንብረት ርክክብ ሥርዓት መኖሩን በተመለከተ፤

71. በተለያየ ምክንያት ስራ የሚለቁ የባንኩ ሰራተኞች በስማቸው የተመዘገቡትን ቋሚ ንብረቶች እንዲያስረክቡ የቁጥጥር እና የክትትል ስርዓት ሊኖርና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

72. ይሁን እንጂ የባንኩ የዲስትሪክት እና የቅርንጫፍ ስራ አስኪያጆች እና ሠራተኞች በኃላፊነት የሚረከቡትን ንብረቶች ሲለቁም ሆነ በዝውውር ሲሄዱ የተረከቧቸውን ንብረቶች በትክክል በቆጠራ የሚያስረክቡበት የቁጥጥር እና የክትትል ስርዓት ባለመኖሩ ስራ አስኪያጆቹ አረካካቢ ሳይኖር ተረካቢው እና አስረካቢው እርስ በእርስ ያለቆጠራ በፊት የተረከበበትን ሰነድ ቲክ ማርክ(✓) በማድረግ የሚረካከቡ መሆኑን በኦዲት ወቅት በአዲስ አበባ ያሉ አራቱም ዲስትሪክቶች፣ ሀዋሳ እና ሻሸመኔ ዲስትሪክቶች እንዲሁም አራት ኪሎ፣ ስላሴ፣ አዲስ አበባ፣ ሰንጋ ተራ፣ መስቀል አደባባይ፣ አዲስ ከተማ፣ ሀዋሳ፣ ታቦር፣ ይርጋለም፣ ነገሌ፣ ሻሸመኔ እና ኦዳ ቅርንጫፎች በአካል ለማየት ተችሏል፡፡ ንብረት የሚያተዳድር ሆነ የሚከታተል ባለሙያ ወይንም ክፍል የተደራጀው በዋናው መ/ቤት እንጂ በዲስትሪክቶችና በቅርንጫፎች የሌለ መሆኑ ታውቋል፡፡

73. ስለሁኔታው የባንኩ ኃላፊዎች ተጠይቀው የንብረት ርክክብ ስርዓት እ.አ.አ ኦገስት 2014 በፀደቀው በባንኩ የFixed and Intangable Asset Managemnet Procedure በመመሪያው ክፍል 2 አንቀፅ 2.2 እና 4.3.2 መሰረት በሁሉም የባንክ አካላት ስር የሚገኙ ሰራተኞች የተረከቧቸውን ንብረቶች የሚያስረክቡበት እና የሚቆጣጠሩበት የተዘረጋ ስርዓት አለ በማለት በቀረበላቸው ነባራዊ ሁኔታ በሰጡት ምላሽ ላይ ገልፀዋል፡፡

74. ኃላፊዎቹ ይህን ቢሉም ተጠያቂነት በሚያሰፍን መልኩ የንብረት ርክክብ ሥርዓት አለመዘርጋቱና ሥራ ላይ አለመዋሉ በኦዲቱ ወቅት በመታወቁ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል አስቸጋሪ ያደርገዋል፡፧

75. በተለያየ ደረጃ ያሉ ኃላፊዎች እና ሠራተኞች በኃላፊነት የሚረከቡትን የባንኩን ንብረቶች በሚዘዋወሩበት ወቅትም ሆነ ባንኩን በሚለቁበት ጊዜ በትክክል በቆጠራ ተረጋግጠ እንዲያስረክቡ ለማድረግ የተዘረጋው የክትትልና ቁጥጥር ተግባራዊ አለመደረጉ የባንኩ ንብረቶች ለስርቆት፣ ለብክነት እና ለብልሹ አስራር ተጋላጭ ያደርገዋል፡፡

ለባንኩ ንብረቶች የጥገና ስርዓት መኖሩን እና ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፧

76. የባንኩ ንብረቶችና ህንጻዎች ብልሽት እና ጉዳት በሚያጋጥማቸው ጊዜ አፋጣኝ ጥገና የሚደረግበት እና መልሰው ሥራ ላይ የሚውሉበት የአሰራር ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

77. ይሁን እንጂ የባንኩ ንብረቶች ሲበላሹ ወቅታዊ ጥገና ስለማይደረግላቸው ለበርካታ ዓመታት በየዲስትሪክቶቹ እና በየቅርንጫፎች ፕሪንተሮች፣ ኮምፒውተሮች፣ የገንዘብ መቁጠሪያ ማሽኖች፣ ፎቶኮፒ ማሽኖች እና ሌሎች የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ እቃዎች ማገልገል የሚገባቸውን ጊዜ ሳያገለግሉ በየቦታው ተከማችተው የተቀመጡ መሆናቸውን በኦዲት ወቅት በባንኩ ዋናው መ/ቤት መጋዘኖች እና በናሙና ተመርጠው በታዩ ዲስትሪክቶች እና ቅርንጫፎች በተደረገ ጉብኝት እና ከተከለሱ መረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

78. ለአብነት፡

- እ.ኢ.አ በ2013/14 ከዋናው መስሪያ ቤት ጋር ተያያዥነት ያላቸው (ተቀፅላ የሆኑ) ብር 160,000 የተገመተ ዋጋ ያላቸው ጥገናዎች 55% ለማጠናቀቅ ታቅዶ 20% ብቻ የተከናወነ መሆኑን፣
- የቢሸፍቱ ቅርንጫፍ እና መኖሪያ ቤት ጥገና በኤልያስ መካሻ የህንፃ ተቋራጭ እንዲሰራና በ300 ቀናት ውስጥ እንዲጠናቀቅ እ.ኢ.አ በግንቦት 15/2014 ከባንኩ ጋር በብር 2,162,334.57 ውል የተዋዋሉ እንዲሁም ተጓዳኝ ስምምነት (Supplimentary Agreement) እ.ኢ.አ በጥር 16/2015 በብር 385,602.66 በድምሩ

በብር 2,547,937.23 ሲሆን ተጓዳኝ ስራውን ጨምሮ ስራው የተጠናቀቀው እ.አ.አ. ነሀሴ 22/2016 መሆኑን ለማየት ተችሏል፡፡ ይህም 456 ቀናት የፈጀ ~~እና~~ እንዲሁም የስራ አፈፃፀም ~~ሙሉ~~ ሪፖርት ላይ እንደታየው ~~ሲታይ~~ 50% ለማጠናቀቅ ታቅዶ 20% ብቻ የተከናወነ መሆኑን፣

- እ.አ.አ በ2015/16 የባንኩ የህንፃና ግንባታ ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ደግሞ ንፋስ ስልክ ህንፃ 30%፣ ናዝሬት ዋናው ቅርንጫፍ ህንፃ 100%፣ አዲስ ከተማ ህንፃ 30%፣ ወሊሶ ቅርንጫፍ እና መኖሪያ ቤት 100%፣ አዳማ ዲስትሪክት ህንፃ 100%፣ መሃልሜዳ ቅርንጫፍ ህንፃ 100%፣ ድሬዳዋ ዋና ቅርንጫፍ 40%፣ ጅማ ቅርንጫፍ 40% እና የመጋዘን ስራ እና የቢሮ ግንባታ (ZAK) 100% ለማከናወን ታቅዶ ምንም የተሰራ ስራ አለመኖሩን፣
- ከ60 በላይ ለሚሆኑ ቅርንጫፎች የጥገና አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ በሚፈልገው ደረጃ አገልግሎቱን መስጠት ባለመቻሉ ፕሪንተሮች፣ የገንዘብ መቁጠሪያ ማሽኖች፣ ፎቶኮፒ ማሽኖች እና ኤቲኤም ማሽኖች በጥቃቅን ብልሽትና መለዋወጫ እጥረት ከአገልግሎት ውጪ ሆነው መጋዘኖችን አጣበው የተቀመጡ መሆኑንበውስጥ ኦዲት ሪፖርት ላይ መገለፁን፣

በኦዲት ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

79. ስለሁኔታው የባንኩ ኃላፊዎች ተጠይቀው፡-

- ከዋናው መ/ቤት ህንፃ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ህንፃዎች (Auxilary buildings) የጥገና ስራ በበጀት አመቱ ለመስራት ታቅዶ የነበረው 100% በተያዘው ዕቅድ መሰረት መጠናቀቁን፣ የቢሾፍቱ ቅርንጫፍ እና መኖሪያ ቤት ህንፃ ጥገና ላይ ተቋራጭ ለመቅጠር ከታቀደው ጊዜ በላይ በመውሰዱና የጥገና ስራውን ለማስጀመር የተቻለው በመጨረሻ ሩብ አመት በመሆኑ አፈፃፀም 20% ብቻ መሆኑን፣ የንፋስ ስልክ ቅርንጫፍ ያለበት ህንፃ ቀድሞ የግንባታ ስራውን የሰራው ተቋራጭ ያልተከፈለኝ ክፍያ አለኝ በማለት ባንኩን ከሶ የነበረ በመሆኑና ይህም ባለበት ስራውን ማሰራት አሳማኝ ባለመሆኑ በበጀት አመቱ ሳይሰራ የቀረ መሆኑን፣ ናዝሬት ቅርንጫፍ ያለበትን ህንፃ አሸናፊው ተቋራጭ ሳይቱን ከተረከበ በኋላ ስራውን በማቋረጡ ምክንያት ውሉ እንዲቋረጥ መደረጉን፣ አዲስ ከተማ ቅርንጫፍ ያለበትን ህንጻ ለመጠገን ጥናት እየተከናወነ ሲሆን ህንፃው በቅርስነት የሚመዘገብ ስለሚሆን በእንጥልጥል የቆየና የጥገና ፈቃድ ለማግኘት ጊዜ የወሰደ መሆኑን፣ ጅማ አብይ

ቅርንጫፍ፣ አዳማ ዲስትሪክት፣ ድሬዳዋ አብይ ቅርንጫፍ እና መሀል ሜዳ ቅርንጫፍ ህንፃዎች ጥገና ጨረታ ወጥቶ መስፈርቱን ያሟሉ ተጫራቾች ማግኘት ባለመቻሉ በበጀት አመቱ ስራው ያልተጀመረ መሆኑን፣

- የገንዘብ መቁጠሪያ እና የፎቶ ኮፒ ማሽኖች ጥገና ስራ ጋር በተያያዘ የመለዋወጫ እቃዎች ከአቅራቢዎች ለማግኘት እጥረት የሚያጋጥም እንዲሁም የባለሙያ እጥረት እንደነበረ ግንዛቤ የተወሰደ በመሆኑ ጥገናዎችን ማከናወን እንዲቻል በየዲስትሪክቱ ያሉ የጥገና ባለሙያዎችን ቁጥር የመጨመር ስራ መሰራቱን እና ችግሩን በዘላቂነት ለመፍታት የጥገና ስትራቴጂክ ጥናት እየተከናወነ መሆኑን፣

በቀረበላቸው ነባራዊ ሁኔታ ላይ በሰጡት ምላሽ ላይ አስተያየት ገልፀዋል፡፡

80. የባንኩ የበላይ ኃላፊዎች ይህን ቢሉም፡-

- እ.አ.አ በ2013/14 የባንኩ የህንፃና ግንባታ ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ላይ ከዋናው መ/ቤት ህንፃ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ህንፃዎች (Auxilary buildings) የጥገና ስራን በተመለከተ ጥገናው መጠናቀቅ በነበረበት ጊዜ ያለው አፈፃፀም 20 በመቶ ብቻ መሆኑን፣
- የጥገና ዕቅዶች ሲታቀዱ ያሉ ችግሮችን አጥርቶ ማቀድ የሚገባ በመሆኑ ችግሮች ሳይታረሙ የሚያዙ ዕቅዶች ለአፈፃፀም ችግር የሚዳርጉ በመሆኑ

የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

81. በባንኩ የተዘረጋው የጥገና ሥርዓት ተግባራዊ ባለመደረጉ በርካታ የባንኩ ንብረቶች ትኩረት ተነፍጓቸው ለብክነት ከመጋለጣቸውም በላይ በቀላሉ በሚጠገኑት ምትክ አዳዲስ ንብረቶች እንዲገዙ በማድረግ ባንኩን አላስፈላጊ ወጪዎችን እንዲያወጣ አድርጎታል፡፡

በባንኩ መጋዘን ውስጥ የንብረቶችን ከፍተኛና ዝቅተኛ የዕቃ መጠን የተወሰነ መሆኑን በተመለከተ፤

82. ባንኩ መጋዘን ውስጥ ለሚያስቀምጣቸው ንብረቶች እንደየባህሪያቸው ዓይነት ዝቅተኛና ከፍተኛ የዕቃ መጠን (Minimum and maximum stock level) ተወስኖ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

83. ይሁን እንጂ ንብረቶች በመጋዘን ውስጥ ዝቅተኛና ከፍተኛ የዕቃ መጠን (Minimum and Maximum Stock Level) ተወስኖ እንዲቀመጥ የሚያስችል የአሰራር ስርዓት አለመኖሩን በኦዲት ወቅት የባንኩን መጋዘኖች በአካል በመመልከት እንዲሁም ከተከለሱት ሰነዶች ለማወቅ ተችሏል፡፡ በመሆኑም

- በቀን 01/6/2008 ዓ.ም ከባህርዳር ዲስትሪክት ለፋሲሊቲ አስተዳደር በተፃፈ ደብዳቤ የተለያዩ ፎርሞች ማለትም Withdrawal፣ pass Book፣ Deposit voucher እና ሂሳብ መክፈቻ ደብተር ባለመኖራቸው በከፍተኛ መጠን እጥረት በመከሰቱ ሥራ ላይ ችግር መፈጠሩን፣
- በ2014/15 ዓ.ም ባንኩ ለሚከፍታቸው 150 አዲስ ቅርንጫፎች በቂ ፕሪንተር እና እስካነር በቁጥር 1591 እና 3921 እያለ ያለው የክምችት መጠን ባለመታወቁ በውስንና በግልፅ ጨረታ 600 ፕሪንተር እና 150 እስካነር የተገዙ መሆኑን፣
- መጋዘን ለሚያዙ ዕቃዎች እንደየባህሪያቸው ዓይነት በተለይም የገንዘብ ማስገቢያ፣ ወጪ ማድረጊያ፣ የሐዋላ እና ሂሳብ መክፈቻ ፎርሞች እንዲሁም ቼኮች በልምድ የሚያዙ እንጂ ዝቅተኛና ከፍተኛ የዕቃ መጠን (Minimum and Maximum Stock Level) እንደ አሰራር ስርዓት ተወስኖ እንደማይሰራበት በአዲስ አበባ የሚገኙ አራቱ ዲስትሪክቶች እና በስራቸው የሚገኙ የተመረጡ ቅርንጫፎች፣ የሀዋሳና የሻሸመኔ ዲስትሪክቶች እና በናሙና ከተመረጡ ቅርንጫፎች

በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

84. ስለሁኔታው የባንኩ ኃላፊዎች ተጠይቀው የክምችትን Minimum Reorder Stock Level ተወስኖ የሚቀመጥበት አሰራር ስርዓት በዋናው ዕቃ ግምጃ ቤት ተተግብሮ የሚሰራበት ሲሆን በቀጣይም በዲስትሪክት ፅ/ቤቶች እና ቅርንጫፎች በቂ ክምችት የሚይዙበትን Minimum Reorder Level አሰራር እየተተገበረ ባለው የERP አሰራር ጭምር በመታገዝ ተግባራዊ የሚደረግ እንደሚሆን በቀረበላቸው ነባራዊ ሁኔታ በሰጡት ምላሽ ላይ ገልፀዋል፡፡

85. በባንኩ ከፍተኛ እና ዝቅተኛ የዕቃ መጠን (Minimum and maximum stock level) አስራር ስርዓት ባለመዘርጋቱ ተፈላጊ የሆኑ አላቂ ዕቃዎች እጥረት እንዲከሰትና

ቀልጣፋ የባንክ አገልግሎት ለደንበኞች ተደራሽ ለማድረግ እንቅፋት ሊሆን ይችላል፡፡

አገልግሎት የሚሰጡ እና የማይሰጡ ንብረቶች አቀማመጥን በተመለከተ፤

86. የሚያገለግሉና የማያገለግሉ የባንኩ ንብረቶች ተለይተው የሚቀመጡበት የአሠራር ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ አገልግሎት አይሰጡም ተብለው የሚቀመጡ የባንኩ ንብረቶች አገልግሎት ሊሰጡ ያልቻሉበት ምክንያት በባለሙያ የሚረጋገጥበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

87. ይሁን እንጂ በርካታ አገልግሎት የሚሠጡና አገልግሎት የማይሰጡ የባንኩ ንብረቶች ሳይለዩ በአንድ ላይ ተቀላቅለው እንደሚቀመጡ እንዲሁም ንብረቶች እንደአይነታቸው ተለያይተው ያልተቀመጡ መሆናቸው ታውቋል፡፡ በተጨማሪም ንብረቶች ለፀሀይ፣ ለዝናብ፣ ለብክነት እንዲሁም ለብልሽት በተጋለጠ ሁኔታ ከመጋዘን ውጭ ተቀምጠው ታይተዋል፡፡ እንዲሁም ንብረቶቹ ተጠግነው አገልግሎት መስጠት አለመቻላቸው ወይም አገልግሎት የማይሰጡበት ምክንያት ያልተገለጸ በርካታ ንብረቶች መኖራቸውን እና ወጥነት ባለው ሁኔታ በባለሙያ የማይረጋገጥ መሆኑን በኦዲት ወቅት ከተሰበሰቡት መረጃዎች እንዲሁም በናሙና ተመርጠው ከታዩት የባንኩ ዲስትሪክቶች፣ ቅርንጫፎች እንዲሁም በዋናው መስሪያ ቤት ባሉ የተለያዩ መጋዘኖች በአካል ለማየት ተችሏል፡፡ ለአብነት የነዳጅ በርሜሎች፣ መወገድ የሚገባቸው ንብረቶች፣ አዲስ የተገዙ ዘመናዊ ፋይል ካቢኔቶች፣ የወንበር፣ የጠረጴዛ ብረቶች እና ሌሎችን በርካታ ንብረቶች የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

ምስል 2. በቫቲካን ኢምባሲ አካባቢ ያለ መጋዘን የንብረት አያያዝ በጥቂቱ

ምስል 3. በአማልጋሚትድ መጋዘን ያሉ ንብረቶች አቀማመጥ በጥቂቱ

ምስል 4. በአማልጋሚትድ መጋዘን ያሉ የባንክ ፎርሞች አቀማመጥ በጥቂቱ

88. ስለሁኔታው የባንኩ ኃላፊዎች ተጠይቀው መወገድ የሚገባቸው ንብረቶች ዕቅድ ተይዞ በመወገድ ላይ ያለ ሲሆን መወገድ የሚገባቸውና ትኩረት የተነፈጋቸው የባንኩ ንብረቶች ተብለው የተዘረዘሩት የገንዘብ መቁጠሪያ ማሽኖች፣ የፎቶ ኮፒ ማሽኖች፣ ፕሪንተሮች፣ ታይፕራተሮች፣ ፎርማቶች፣ ብዛት ያላቸው ጥራዞች፣ አሮጌ መኪናዎች፣ የመኪና መለዋወጫዎች፣ የተሰባበሩ ወንበሮች፣ ጠረጴዛዎች እና ጊዜ ያለፈባቸው ፎርማቶች በጨረታ እንዲሸጡ እንደተደረገ እና ንብረቶች አገልግሎት የማይሰጡና የሚሰጡ ተብለው በባንኩ ባለሙያዎች ከታዩ በኋላ ከአገልግሎት ውጭ

የሆኑት ወደ ዕቃ ግ/ቤት የሚላኩበት አሰራር ያለ ቢሆንም ባለፉት ዓመታት ከባንኩ ከፍተኛ የቅርንጫፎች ቁጥር መጨመር ጋር ተያይዞ በአሠራሩ መሠረት በሁሉም ቅርንጫፎች በወጥነት እየተተገበረ አለመሆኑን ገልጸዋል፡፡ በመሆኑም ይህንን ግድፈት ለመቅረፍ የአገለገሉ ንብረቶች የሚለዩበትን እና የሚወገዱበት አሠራር መመሪያ እየተከለሠ የሚገኝ ሲሆን ለዚሁ ዓላማ የሚያገለግል መጋዘን ተለይቶ እድሳት እየተደረገለትና የሰው ኃይል እየተደራጀ ይገኛል በማለት በቀረበላቸው ነባራዊ ሁኔታ በሰጡት ምላሽ ላይ ገልፀዋል፡፡

89. የአገለገሉ ንብረቶች የሚለዩበትን እና የሚወገዱበት አሠራር በተመለከተ እየተከለሰ ነው የተባለው መመሪያ ማስረጃ ያልቀረበና የንብረት አያያዝና አጠባበቅ እንዲሁም አወጋገድ ላይ ከፍተኛ ችግር የሚታይ በመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

90. የሚያገለግሉና የማያገለግሉ የባንኩ ንብረቶች አንድ ላይ የሚቀመጡበት ሁኔታ መኖሩ የሚያገለግሉ ንብረቶች አቀማመጥን ሥርዓት ለማስያዝ ችግር የሚፈጥር እና የሚያገለግሉ ንብረቶችን በቀላሉ ማግኘት እንዳይቻል ያደርጋል፡፡

በባንኩ በዕዳ የተወረሱ ንብረቶችን አስተዳደርን በተመለከተ፤

91. ባንኩ በዕዳ የተያዙ ንብረቶችን በውርስ የራሱ ለማድረግ ሲወስን የባለቤትነት መብቱን በፍጥነት ለማዘዋወር የሚያስችለው የአሰራር ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ ባንኩ በተለያየ ሥፍራ የሚገኙትን (የዋናው መስሪያ ቤትና ዲስትሪክት ቢሮዎች) በዕዳ የተያዙ ንብረቶቹን ተሸጠው ዕዳው እስኪከፈል ወይንም ባንኩ ለራሱ አገልግሎት እስኪውል ድረስ ንብረቶቹ ይዞታቸው እየተረጋገጠ በባንኩ አመታዊ የንብረት ቆጠራ ከተገኘው የቋሚ ንብረት መዝገብ ጋር በዓመት ሁለት ጊዜ ማስታረቅ ይኖርበታል፡፡

92. ይሁን እንጂ ባንኩ በእዳ የወረሳቸው በርካታ ቋሚ ንብረቶች እንዳሉ፣ የሚደረግላቸው እንክብቃቤ ጠንካራ አለመሆኑን እና በወቅቱ ሊሸጡ እንዳልተቻሉ፣ ንብረቶቹ ከቆጠራ ጋር ወጥነት ባለው መልኩ የማይታረቁ መሆኑን በኦዲት ወቅት ከተሰበሰበው መረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡

93. በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው ከታዩት፡

- በሐዋሳ ዲስትሪክት በዕዳ የተወረሱ (Acquired Assets) አስራ ስምንት (18) ቤቶች አጠቃላይ ዋጋቸው ብር 1,965,298.15 እንደሚገኙ፣
- በሻሸመኔ ዲስትሪክት በዕዳ የተወረሱ ስምንት ቤቶች በብር 448,533.43 ሲኖሩ ሰባት ቤቶች ሳይሸጡ የቆዩ መሆኑን እና ቀሪው አንድ ቤት ከአዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ በብድር ምክንያት ለመሸጥ አለመቻሉ፣
- በአዲስ አበባ ከተማ በመጋቢት 14 ቀን 2003 ዓ/ም በወረዳ 7 ቀበሌ 30 የቤት ቁጥር 913 የሆነው ቤት በዕዳ መያዣነት በብር 298,781.16 የተያዘና ቤቱ በባንኩ አዲስ አበባ ቅርንጫፍ ስር የሚገኝ ሲሆን፣ ይህን ቤት የተከራየው አካል የውሉን ጊዜ ከጨረሰ በኋላ የዋጋ ማስተካከያ ሳይደረግና ጨረታ በግልፅ ሳይወጣ ተከራዩ ለሌላ አካል እንዲከራይ ያደረገ መሆኑ፣
- ባንኩ ህዳር 26 ቀን 1998 ዓ.ም ባንኩ በእዳ ማካካሻነት የወረሰው የቀድሞ የብራሌ እርሻ ልማት እና አዲስ አበባ ከተማ የሚገኘው የጥጥ መዳመጫ ፋብሪካ የመነሻ ዋጋው ብር 86,697,432.24 እና የእርሻው ስፋት 5640 ሄክታር ሲሆን እስከ ህዳር 2008 ዓ/ም በዓመትብር 5,650,000 ለ10 አመታት ተከራይቶ የነበረ ሲሆን አሁን የኪራይ ዘመኑ ያለቀ በመሆኑ ተከራይቶት የነበረው ኦሞ ሸለቆ አግሮ ኢንደስትሪ ኃ/የተ/የግ/ማህበር በቀን 13/12/08 ዓ.ም ለባንኩ በፃፈው ደብዳቤ ንብረቱን ባንኩ እንዲረከበው ቢፅፍም ባንኩ ግን አፋጣኝ መልስ እንዳልሰጠውና በአስቸኳይ ንብረቱን ካልተረከበው ድርጅቱ ንብረቱ ላይ ለሚፈጠረው ነገር ኃላፊነት እንደማይወስድ የገለፀ መሆኑን፤ ባንኩ ይህን ተከትሎ የብራሌ እርሻ መሬትን ለማከራየት የተለያዩ ጨረታዎች ቢያወጣም እስከ 12/04/09 ዓ.ም ድረስ እንዳልተከራየና ከስድስት ወራት በላይ ያለኪራይ ድርጅቱ የተጠቀመ መሆኑ፣
- በ2007 ዓ/ም በጥቅምትና በየካቲት ወር የማስታረቅ ስራ የተሰራ ሲሆን፣ በ2006 ዓ/ም ግን በነሀሴ ወር አንድ ጊዜ ብቻ የማስታረቅ ስራ የተከናወነ መሆኑ፤ በ2008 ዓ/ም ግን ምንም የማስታረቅ ስራን የሚያሳይ ሪፖርት ተጠይቆ ለኦዲት አለመቅረቡ፣
- በየካቲት 17 ቀን 2007 ዓ/ም ከባንኩ በዕዳ የተረከባቸው ንብረቶች አስተዳደር ለሁሉም ዲስትሪክቶች በተፃፈ ደብዳቤ ስር የተገለፁ ዝርዝሮች እንደሚያሳዩት በጂማ፣ መቀሌ፣ ናዝሬት፣ ወላይታ፣ ባህርዳር፣ ደሴ፣ ድሬዳዋ፣ ሰሜን አዲስ አበባ፣ ምዕራብ አዲስ አበባ፣ ነቀምት እና ደቡብ አዲስ አበባ ዲስትሪክቶች

አጠቃላይ ብር 4,131,601.27 የሆኑ ንብረቶች በባንኩ በዕዳ የተረከባቸው ንብረቶች አስተዳደር ምዝገባ (ባላንስ) ላይ የማይታዩ ሆነው ሳለ በፋይናንስ ምዝገባ (ባላንስ) ላይ ግን የሚታዩ ወይም ያልተቀነሱ መሆናቸው፣

በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

94. ስለሁኔታው የባንኩ ኃላፊዎች ተጠይቀው፡-

- ከአዲስ አበባ ውጪ ያሉ ዲስትሪክቶች ንብረቶችን የመሸጥ፣ የማከራየት እና በአጠቃላይ የማስተዳደር ኃላፊነት የተሰጣቸው ሲሆን የሚታዩ ክፍተቶችን ለመሙላት ክፍላችን የበኩሉን እገዛ በቀጣይ የሚያደርግ መሆኑን፣
- በሐዋሳ ዲስትሪክት የሚገኙ በዕዳ የተወረሱ (Acquired Assets) አስራ ስምንት (18) ቤቶች ባንኩ ባለው መመሪያ መሰረት ለመሸጥ ጥረት ቢያደርግም በአካባቢው ከረጅም ጊዜ ጀምሮ የሚታየው ተጨባጭ ሁኔታ ንብረቶቹን ባለው መመሪያ ላይ ብቻ ተመርኩዞ በዝግ ወይም በግልጽ ጨረታ ለመሸጥ አስቸጋሪ ስለሆነ እነዚህ ንብረቶች በልዩ ውሳኔ ለባንኩ አገልግሎት የሚጠቅሙትን ወደ ባንኩ ስም እንዲዞር ተደርጎ እንዲያገለግል የተደረገ ሲሆን በሌሎቹ ንብረቶች ላይ ባንኩ እየተከተለ ያለው አካሄድ የዲስትሪክቱ፣ የቅርንጫፉን እና የአካባቢውን መስተዳድር ፍላጎት ታሳቢ በማድረግ ስለሆነ ንብረቶቹን በአጭር ጊዜ ውስጥ በሽያጭ ማስወገድ ሳይቻል መቅረቱን
- በሻሸመኔ ዲስትሪክት ስር የሚገኙ 8 ቤቶች በዲስትሪክቱ በኩል በተደጋጋሚ ለመሸጥ ጥረት ቢደረግም ገዥ ባለመገኘቱ ንብረቶቹ ሊሸጡ ያልቻሉ፣ ንብረቶቹ በሂደት ሊሸጡ የሚችሉ ቢሆንም በዋናነት የንብረቶቹን ሁኔታ በባለቤትነት እያስተዳደረ የሚገኘው ዲስትሪክት ተከታትሎ ሌሎች አማራጮችን በመዳሰስ የመጨረሻ እልባት የሚያገኙበትን ሁኔታ መፍጠር የሚኖርበት መሆኑን እና ከአዋሽ ባንክ ጋር የተገናኘውን ንብረት በተመለከተ አዋሽ ባንክ በዋስትና እንደያዘውና እንደሚገባው ክስ በመመስረቱ ጉዳዩ በዲስትሪክቱ ነገረፈጅ በኩል ክትትል ቢደረግበትም የሚመለከተው ፍርድ ቤት ቤቱ ለአዋሽ ባንክ እንደሚገባ መወሰኑን
- በአዲስ አበባ ከተማ በወረዳ 7 ቀበሌ 30 የቤት ቁጥር 913 የሆነውን ቤት በተመለከተ ተከራይ ያለባቸውን የ18 ወራት ውዝፍ ኪራይ እንዲከፍሉ ቢጠየቁም ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ቅርንጫፉ ቤቱን በህገወጥ መንገድ

ከተከራይ ተከራይተው ለነበሩት ግለሰብ በቀድሞው የኪራይ ዋጋ ለማከራየት ሲወስን ቤቱ መቼ እንደሚፈርስ ባለመታወቁ፣ ተከራዩ በሂደት ውዝፍ ሂሳባቸውን የከፈሉ በመሆናቸውና ሌሎች ምክንያቶችን መሰረት በማድረግ መሆኑን እና ይህን አይነት ችግር እንዳልተደገመ የገለፁ ሲሆን አሁን ቤቱ ጨረታ ወጥቶ በብር 21,100 ተከራይቶ መገኘቱን፣

- የቀድሞ ብራሌ እርሻ ልማት ድርጅትን በተመለከተ የቀድሞው ተከራይ ንብረቱን ባንኩ እንዲረከበው የጠየቀ ቢሆንም ድርጅቱ ከአካባቢው ህብረተሰብ እና መስተዳድር ጋር ያለውንና የገነባውን መልካም ግንኙነት ታሳቢ በማድረግ ባንኩ ንብረቱን ተረክቦ ለአዲሱ ተከራይ እስኪያስረክብ ድረስ የንብረቱን ጥበቃ እንዲያከናውን ከባንኩ የበላይ አካል በተሰጠ አቅጣጫ መሰረት ንብረቱን ባንኩ ሳይረከብ ቆይተናል፡፡ ነገር ግን ድርጅቱ በ2008 ዓ.ም ንብረቱን ከመጠበቅ እና ባለፈው የእርሻ ወቅት የዘራውን ሰብል ከመሰብሰብ የዘለለ በእርሻ ልማቱ ላይ ያለማው ምንም ነገር የሌለ እና ባንኩም ያንን ያልፈቀደ እንደሆነ፣ በአሁኑ ወቅት ባንኩ ንብረቱን ከቀድሞው ተከራይ ተረክቦ ለክልሉ ምርጥ ዘር ድርጅት እያስረከበ መሆኑን፣
- በየካቲት 17 ቀን 2007 ዓ/ም የታዩ ልዩነቶች እንዳሉ ሊቆዩ የቻሉበት ምክንያት በዲስትሪክቶች ወይም በክፍላችን ንብረቶች ከተሸጡ በኋላ የሽያጭ ገንዘብ በትክክለኛው ሂሳብ ቁጥር መግባት ሲገባው ባለመግባቱ እንዲሁም የሂሳብ አሰራሮችን ጠንቅቆ ባለማወቅ ሲሆን ክፍተቶች ለይቶ ትክክለኛውን ትራንዛክሽን ለማሳለፍ ረጅም ጊዜ ስለሚፈጅና አብዛኛዎቹም የቆዩ በመሆናቸው እንዲሁም አንዳንድ ቅርንጫፎች ላይ የሚታይ ግዴለሽነትና ትኩረት ያለመስጠት ለችግሩ አስተዋጽኦ እንዳደረገና እነዚህን ልዩነቶች የማጥራት ሥራ በቀጣይነት በመካሄድ ላይ ይገኛል፡፡ በ2008 ዓ.ም ምንም ዓይነት ሂሳብ የማስታረቅ ስራ አልተሰራም የተባለውን በተመለከተ ውጤታማ የሆነ ሒሳብ የማስታረቅ ስራ የተሰራው በዚህ ዓመት መሆኑን፣

በቀረበላቸው ነባራዊ ሁኔታ በሰጡት ምላሽ ላይ ገልፀዋል፡፡

95. የበላይ ኃላፊዎቹ ይህን ምላሽ ቢሰጡም ዲስትሪክቶች የራሳቸው ንብረትን የማስተዳደር ስልጣን ቢኖራቸውም ዋናው መ/ቤት ንብረቶቹ በምን መልኩ እንደተያዙ መከታተልና መቆጣጠር የሚያስፈልገው በመሆኑ እንዲሁም

ዲስትሪክቶቹና ቅርንጫፎቹ እነዚህን ንብረቶች በሂሳብ መግለጫቸው በትክክለኛው መንገድ እያሳዩ መሆኑን ማረጋገጥ የሚገባው በመሆኑ እና ይህም የባንኩን አጠቃላይ የሂሳብ መግለጫ ላይ ተጽዕኖ ስለሚያሳድር ኃላፊነቱ የቅርንጫፎችና ዲስትሪክቶች ነው በማለት መተው ተገቢ ባለመሆኑ፣ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

96. በዕዳ የተያዙ ንብረቶች በወቅቱ ባለመሸጣቸው በብድር የተሰጠውን ገንዘብ ሳይመልሱ ባንኩን ለኪሳራ ሊዳርጉት ይችላሉ፡፡ በተጨማሪም ንብረቶቹ ከሌላው ቋሚ ንብረቶች ጋር በየጊዜው የማይታረቁ ከሆነ የባንኩ የሂሳብ መግለጫ ትክክለኛውን ገጽታ እንዳያሳይ ሊያደርግ ይችላል፡፡

2.2.2 የንብረት አወጋገድ ስርዓት መኖሩንና ተግባራዊ ስለመሆኑ፤

መወገድ የሚገባቸው የባንኩ ንብረቶችን በተመለከተ፤

97. አገልግሎት የማይሰጡ የባንኩ ንብረቶች የሚወገዱበት የአወጋገድ ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

98. ይሁን እንጂ፡

- የባንኩ አወጋገድ መመሪያ በ1999 ዓ/ም የወጣ ቢሆንም የባንኩን ወቅታዊ ሁኔታ እና አሰራር ጋር እንዲጣጣም ተደርጎ ያልተከለሰ መሆኑ፣ በተጨማሪም ባንኩ መወገድ የሚገባቸውን ንብረቶች በተመለከተ ዓመታዊ ዕቅድ የሌለው መሆኑ ታውቋል፡፡
- በናሙና ተመርጠው በታዩት ቫቲካን፣ ጃቲ፣ አማልጋሜትድ መጋዘኖች፣ በምስራቅ አዲስ አበባ ዲስትሪክት መስቀል አደባባይ ቅርንጫፍ፣ በአዋሳ እና ሻሸመኔ ዲስትሪክቶች እንዲሁም ቅርንጫፎች መወገድ የሚገባቸው እና ትኩረት የተነፈጋቸው የተለያዩ የባንኩ ንብረቶች ከአገልግሎት ውጪ ~~ዩሆኑ~~ ሆነው እና ለረጅም ጊዜ በንብረት መጋዘን ውስጥ ተቀምጠው ~~የተቀመጡ~~ እንዲሁም ከመጋዘን ውጪ ተጥለው የሚገኙ መሆኑ፣



ምስል 5፡- በአማልጋሜትድ እና ቫቲካን ኢምባሲ አካባቢ ባሉ የባንኩ መጋዘኖች የንብረት አቀማመጥ የሚያሳይ በጥቂቱ

- የባንኩ የአወጋገድ መመሪያ በክልል ያሉ ዲስትሪክቶች አገልግሎት የማይሰጡ ንብረቶችን በራሳቸው ማስወገድ እንደሚችሉ ቢያስቀምጥም እንዲወገዱ ያልተደረገ መሆኑ፣
- የባንኩ ዲስትሪክቶችና ቅርንጫፎች አገልግሎት የማይሰጡ የባንኩ ንብረቶች በማዕከል ደረጃ እንዲቀመጥ ለዋናው የባንኩ ንብረት አስተዳደር እና ለመጋዘን በደብዳቤ ቢያሳውቁም ምላሽ ያልተሰጣቸው መሆኑ፣

በኦዲት ወቅት ከተከለሱ መረጃዎች፣ በመስክ ጉብኝት እና ከኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

99. ስለሁኔታው የባንኩ ኃላፊዎች ተጠይቀው ባንኩ የንብረት አወጋገድ መመሪያ ክለሣ በሂደት ላይ እንደሚገኝ እና አገልግሎት የማይሠጡ ዕቃዎች የሚሠበሠቡበት እና ለማስወገድ በሚመች መልኩ የሚቀመጡበት መጋዘን በ2009 ዓ.ም. በዕዳ ማካካሻነት ከተረከበው ንብረት መካከል የመረጠ ሲሆን ለዚሁ ዓላማ አገልግሎት ላይ እንዲውል በጥገና ላይ ይገኛል በማለት በቀረበላቸው ነባራዊ ሁኔታ በሰጡት ምላሽ ላይ ገልፀዋል፡፡

100. ባንኩ አገልግሎት የማይሰጡ ንብረቶችን በወቅቱ የሚያስወግድበትን አሰራር ተግባራዊ ባለማድረጉ የተበላሹና ጥቅም የማይሰጡ ንብረቶች በባንኩ መጋዘኖች በብዛት በመቀመጣቸው የቦታ ጥበት እንዲከሰትና ከአቀማመጥ ችግር የበለጠ እንዲበላሹ ያደርጋል፡፡

2.3 የባንኩ የግዥና ንብረት አስተዳደርን በተመለከተ የመረጃ አያያዝ ስርዓት መኖሩን መገምገም

በባንኩ ለሚከናወኑ ግዥዎች የገበያ ጥናት መከናወኑን በተመለከተ፤

101. ባንኩ ለሚያከናውናቸው ግዥዎች መደበኛ የሆነ የገበያ ጥናት ማከናወን አለበት፡፡ ጥናቱንም መሰረት በማድረግ አመላካች የእቃዎች የዋጋ ዝርዝር (Indicative Price List) ሊያዘጋጅ እና በየጊዜው ወቅታዊ ሊያደርገው ይገባል፡፡

102. ይሁን እንጂ፡

- የባንኩ የግዥ አፈፃፀም መመሪያ አንቀፅ 12 ንዑስ አንቀፅ 12.1 ባንኩ ለሚያከናውናቸው ግዥዎች እንዲሁም ከአቅራቢዎች ጋር ለሚመሰርታቸው ዘላቂ ግንኙነቶች ግብዓት ወይም አመላካች የሆነ የገበያ ጥናት በማከናወን

አመላካች የዋጋ ዝርዝር (Indicative Price List) ለማዘጋጀት እንደሚረዳ የተገለፀ ቢሆንም ጥናቱ ያልተከናወነ መሆኑን፣

- የረጅም ጊዜ ውል ግዥ በሚፈፀምበት ጊዜ ባንኩ ያከናወነውን የገበያ ጥናት መሰረት በማድረግ የዋጋ ማስተካከያ እንደሚደረግ የባንኩ የግዥ አፈፃፀም መመሪያ በአንቀፅ 25.6 ላይ የሚጠቅስ ቢሆንም የገበያ ጥናት ባለመኖሩ ትክክለኛ የዋጋ ማስተካከያ ለማድረግ የሚያስቸግር መሆኑን

በኦዲቱ ወቅት ለመገንዘብ ችለናል፡፡

103. ስለሁኔታው የባንኩ የፋሲሊቲ አስተዳደር የሥራ ሃላፊዎች በሰጡት ምላሽ ግዥዎችን ለማከናወን ለበጀት መነሻ የሚሆን የዋጋ ጥናት እንደሚያደርጉ ነገር ግን የግዥ አይነቶች በአይነትም ከ150-200 የሚደርሱ በመሆኑ ለእያንዳንዳቸው የገበያ ጥናት ማካሄድና የተጠቃለለ ነገር ማቅረብ እንደሚከብድ ገልፀዋል፡፡

104. ስለሁኔታው የባንኩ ኃላፊዎች ተጠይቀው ባንኩ በየዓመቱ አወዳድሮ ካከናወናቸው ግዥዎች አሸናፊ ዋጋን መነሻ በማድረግ በቀጣይ አመት ለሚያከናወነው ግዥ ሊኖር የሚችለውን የዋጋ ጭማሪ ታሳቢ አድርጎ በመጨመር ለቀጣይ በጀት አመት አመላካች/መነሻ የሚሆነውን ዋጋ (Indicative Price List) የግዥ መመሪያውን አንቀጽ 12.1.1 እና "ሀ" መሰረት በማድረግ ከተከናወኑ ግዥዎች መረጃውን በመሰብሰብ ስራ ላይ ይውላል፡፡ የረዥም ጊዜ ውል የተዋዋልንባቸው ውስን ዕቃዎች ሲሆኑ ከአቅራቢው ጋር ድርድር በማድረግ ከላይ በተጠቀሰው መንገድ ግዥው ይከናወናል በማለት በቀረበላቸው ነባራዊ ሁኔታ ላይ በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል፡፡

105. የባንኩ ኃላፊዎች ይህንን ቢሉም በተሰጠው መልስ ላይ የተጠቀሰው አንቀፅ 12.1.1 እና "ሀ" የገበያ ጥናቱ በሚካሄድበት ወቅት ሊካተቱ የሚገባቸው መሰረታዊ ነጥቦች ናቸው በሚል የተጠቀሱ እንጂ ራሳቸውን ችለው ግዥ ሊከናወንባቸው የሚገባ አሰራሮች ባለመሆናቸው፣ እንዲሁም በረጅም ጊዜ ውል ግዥ ላይ የሚከናወነውን የዋጋ ማስተካከያ በተመለከተ የገበያ ጥናቱ ባልተከናወነበት ሁኔታ የዋጋ ማስተካከያ ተደርጓል ለማለት የሚያስቸግር እና የንጽጽር የተደረገበትም ማስረጃ ለኦዲት ባለመቅረቡ የተሰጠውን መልስ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

106. በባንኩ መደበኛ የሆነ የገበያ ጥናት ባለማከናወኑ በሚገዙ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ዋጋ ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድርበት ሁኔታ መኖሩ እንዲሁም የዋጋ ማስተካከያ

ለሚያስፈልጋቸው ግዥዎች ትክክለኛ የዋጋ ማስተካከያ ማድረግ ኢኮኖሚያዊ ግዥ ማከናወን እንዳይቻል ያደርጋል፡

የባንኩን የዕቃ አቅራቢዎች ዝርዝር ወቅታዊ መደረጉን በተመለከተ፤

107. ባንኩ የአቅራቢዎችን የብቃት ደረጃ በመለካት የአቅራቢዎች ዝርዝር ሊያዘጋጅ እና በየሁለት አመቱ ዝርዝሩን በመከለስ ለሚመለከታቸው አካላት አቅርቦ በማፀደቅ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

108. ባንኩ የሚያከናውናቸው ግዥዎች ላይ የሚሳተፉ የአቅራቢዎች ዝርዝር አዘጋጅቷል፡፡ ነገር ግን

- የአቅራቢዎች ዝርዝር በየሁለት ዓመት መከለስ እንዳለበት የተገለፀ ቢሆንም ለ2015/16 ግዥ ለባንኩ የተላከው የመኪና አቅራቢዎች ዝርዝር እ.አ.አ የ2013 (2005 ዓ/ም) እንደሆነ እንዲሁም እ.አ.አ 2013 ዓ.ም ግዥ የተላከው የመኪና አቅራቢዎች ዝርዝር የተዘጋጀው እ.አ.አ በ2009 (በ2001 ዓ/ም) መሆኑን፣
- የባንኩ የግዥ አፈፃፀም መመሪያ አንቀፅ 55 ንዑስ አንቀፅ 55.3 ላይ ባንኩ በሚያወጣው ጨረታ ላይ የሚሳተፍ ማንኛውንም አቅራቢ ወይም ተጫራች ለመቀበል በቂና በተሟላ መልኩ ስለእያንዳንዱ ተጫራች ተገቢውን መረጃ መያዝ እንደሚኖርበት የሚገልፅ ቢሆንም በናሙና ተመርጠው በተመለከትናቸው የጨረታ ሰነዶች ላይ የሚቀርቡም ሆነ የሚያሸንፉ አቅራቢዎች ባንኩ ባዘጋጀው የአቅራቢዎች ዝርዝር ላይ ስለመኖራቸው የተረጋገጠበት ማስረጃ እንዲሁም ሌሎች ተያያዥ ማስረጃዎችን በተሟላ ሁኔታ የማያያይዙ መሆኑን፣ (ዝርዝሩ በአባሪ 3 ተያይዟል፡፡)
- እ.አ.አ በታህሳስ 2, 2013 ከባንኩ ጤና ክሊኒክ በተጠየቀ መጠየቂያ ላይ ባንኩ በበመድኃኒት አቅራቢነት በዝርዝር ከያዛቸው አቅራቢዎች መግዛት ሲገባው በክሊኒኩ ሀላፊ መድሀኒቱ የሚገዛባቸው አቅራቢዎች ዝርዝር ቀርቦ በቀረበው ዝርዝር መሰረት መድሀኒቱ እንዲገዛ የተደረገ መሆኑን፣

በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

109. ስለሁኔታው የባንኩ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፡-

- የመኪና ግዥ ላይ የአቅራቢዎች ዝርዝርን በተመለከተ በትራንስፖርት ሚኒስቴር የትራንስፖርት ባለሥልጣን የሚዘጋጀውን መኪና ለመስመጣት/ለማቅረብ ፈቃድ በተሰጣቸው እና በቅርብ ጊዜ የአቅራቢዎች ዝርዝር የግዥው ሂደት የተከናወነ መሆኑ፣ በ2006 ዓ/ም የባንኩ የውስን አቅራቢዎች ዝርዝር የተከለሰ ሲሆን በ2008 ክለሳ ያልተከናወነ መሆኑ፤ ሆኖም በ2009 ክለሳ በማከናወን ሂደት ላይ እንደሚገኙ እንዲሁም ግልጽ ጨረታን በተመለከተ ተጫራቾች ተገቢ ማስረጃዎችን በማያያዝ የጨረታ ሠነዱን መውሰድ የሚችሉ ሲሆን አስፈላጊ ሠነዶች ስለማቅረባቸው ከጨረታው ከተከፈተ በኋላ በሚከናወነው ግምገማ በቅድመ ሁኔታ የሚገመገም እንደሆነና ያልቀረቡ ማስረጃዎች ቢኖሩ በመንግሥት የግዥና ንብረት አስተዳደር ድረገጽ ላይ ስለመመዝገባቸው ማጣሪያ የሚደረግ መሆኑን፣
- የመድኃኒት ግዥን በተመለከተ የግዥ ሂደቱ የተጀመረው በነባራዊ ሁኔታው ላይ እንደተጠቀሰው ሳይሆን ባንኩ በውስን የመድኃኒት አቅራቢነት ለተመዘገቡት 25 አቅራቢዎች የዋጋ ማቅረቢያ መሰብሰቢያ የበተነ ሲሆን ከተጠየቁት የመድኃኒት ዓይነቶች መካከል የተወሰኑ መድኃኒቶች በሁሉም የተጋበዙ አቅራቢዎች ሊገኙ ባለመቻላቸው መድኃኒቱን በገበያ ላይ ከሚገኙ አቅራቢዎች በድጋሚ የዋጋ ማቅረቢያ ተሰብስቦ መግዛት እንዲያስችል የጤና ማዕከሉ መድኃኒቱን ሊይዙ የሚችሉ አቅራቢዎችን እንዲያመላክት በተጠየቀው መሰረት 11 አቅራቢዎችን መረጃ የጠቆመና በግዥ ሂደት ዋጋ ማቅረቢያ ላልተመለሰላቸው (no proforma available) መድኃኒቶችን ለማሟላት/ግዥ ለመፈጸም በድጋሚ የዋጋ ማቅረቢያ ግዥ የተከናወነ ሲሆን በአጠቃላይ የግዥው ሂደት በገበያው ላይ ያሉትን አቅራቢዎች ዳሰሳ የተደረገበት መሆኑን

በቀረበላቸው ነባራዊ ሁኔታ ላይ በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል፡፡

110. ኃላፊዎቹ ይህን ምላሽ ቢሰጡም

- የአቅራቢዎች ዝርዝርን በተመለከተ በሁለቱ አመታት ማለትም እ.አ.አ በ2015/16 እና 2013 ወቅታዊ ያልሆነ የመኪና ዝርዝር የቀረበ በመሆኑ፣
- በግልፅ ጨረታ ለውድድር የሚቀርቡ አቅራቢዎች ማስረጃዎችን በተገቢው ሁኔታ እንደማያያይዙ እንዲሁም

- የመድሀኒት ግዥውን በተመለከተ በመጀመሪያ በውስን ለ25 አቅራቢዎች መድኃኒቱን ለመግዛት ጥረት የተደረገበት ማስረጃ ለኦዲቱ ያልቀረበ በመሆኑ

የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

111. ባንኩ የአቅራቢዎችን ዝርዝር በየጊዜው ወቅታዊ አለማድረጉ በየጊዜው መስፈርቱን ያሟሉ አቅራቢዎችን ለማካተትም ሆነ ግዴታቸውን ያልተወጡትን አቅራቢዎች ለማስወጣት እንዳይችል እና ውድድሩ ፍትሃዊ እንዳይሆን ከማድረጉም በላይ የግዥ መመሪያውን በመተላለፍ ተጠቃሚዎች በሚሰጡት ጥቆማ የሚፈጸም ግዥ ህገወጥ አሰራር እና ለሙስና በር የሚከፍት ነው፡፡

ወቅታዊ የሆነ የመረጃን ልውውጥንና አደረጃጀትን በተመለከተ፤

112. ቅርንጫፎችና ዲስትሪክቶች ስለባንኩ ንብረቶች ሙሉና ወቅታዊ መረጃ ለዋናው መስሪያ ቤት በየወሩ ሊልኩ ይገባል፡፡ ባንኩ የግዥ እና ንብረት አስተዳደርን በተመለከተ ማስረጃዎችን በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሊያደራጅ ይገባል፡፡

113. ይሁን እንጂ፡

- በአመት ሁለት ጊዜ ከሚደረገው የቆጠራ ሪፖርት እና የተበላሹ ዕቃዎችን እንዲነሱ ከመጠየቅ በስተቀር ንብረትን በተመለከተ ወቅታዊነቱን በጠበቀና በቋሚነት ለዋናው መስሪያ ቤት የሚላክ ሪፖርት አለመኖሩን እንዲሁም በየዲስትሪክቶችና በየቅርንጫፎች የንብረትን ሁኔታ የሚቆጣጠርና ወቅቱን የጠበቀ ሪፖርት ለዋናው መስሪያ ቤት የሚያቀርብ ባለሙያ ባለመኖሩ ስራውን መስራት አለመቻሉን፣
- የባንኩ የግዥ እና ንብረት አስተዳደር መረጃዎች በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ያልተደገፉ በመሆናቸው በተደጋጋሚ አንድ ፋይል ኮፒ እየተደረገ መያዙ (ከ15 ጊዜ በላይ ኮፒ የተደረገ ለመጥቀስ ጨረታ ቁጥር 16/2013/14)፣ የሚታሰሩት ፋይሎች ቅደም ተከተል የሌላቸው መሆኑ፣ ፋይሎች በተሟላ መልኩ የማይታሰሩ መሆኑ፣ ተያያዥነት የሌላቸውን ማስረጃዎች በአንድ ላይ ማሰር፣ ተመሳሳይና ከሰባት በላይ የሚሆኑ ዋና (Original) ደብዳቤዎች በተደጋጋሚ በአንድ ሀላፊ ተፈርመው መያያዛቸውን (ለመጥቀስ ጨረታ ቁጥር 03/2013/2014)፣
- በአብዛኛው የባንኩ ግዥዎች የጨረታውን ሂደት የሚያሳዩ ቃለ ጉባኤዎች የሌሉ እና አልፎ አልፎ ያሉትም የጨረታ ቃለ ጉባኤዎች የጨረታውን ሂደትና

የተደረሰበትን ውሳኔ በግልጽ እና በዝርዝር የሚያሳዩ አለመሆናቸው (ዝርዝሩ በአባሪ 3 ተያይዟል)

- የሚወገዱ ንብረቶች ዝርዝር ተለይተው እና ወቅታዊነታቸውን በጠበቀ ሁኔታ ተመዝግበው አለመገኘታቸውን፣

በኦዲቱ ወቅት ለመረዳት ችለናል፡፡

114. ስለሁኔታው የባንኩ ኃላፊዎች ተጠይቀው በባንኩ የfixed & Intangible Asset MGT መመሪያ ክፍል ስድስት አንቀጽ ii መሠረት ቅርንጫፎች እና የዋናው መ/ቤት አካላት በየስድስት ወር በእጃቸው የሚገኙትን ንብረቶች ቆጠራ አከናውነው እና ከማህደር ጋር አስታርቀው ለፋይናንስ የሥራ ሂደት ይልካሉ፡፡ በአሁኑ ወቅት ባንኩ የግዥ እና ንብረት አስተዳደር ሥርዓቱን ለማዘመን የERP ሶፍትዌር ዝርጋታ በትግበራ ላይ ይገኛል፡፡ በመሆኑም የተገኘው ግድፈት በዚሁ የሚስተካከል ይሆናል በማለት በቀረበላቸው ነባራዊ ሁኔታ በሰጡት ምላሽ ላይ ገልፀዋል፡፡

115. በባንኩ ያሉ ንብረቶችን መረጃ በየጊዜው ሙሉና ወቅታዊ አለመደረጉ እና በዘመናዊ ቴክኖሎጂ አለመደገፉ ወቅታዊ መረጃ እንዳይኖርና ለቁጥጥር እና ለክትትል አመቺ እንዳይሆን እንዲሁም ባንኩ ሁሉን ነገር በወረቀት መስራቱ አላስፈላጊ ወጪዎችን እንዲያወጣ አድርጎታል፡፡

ክፍል ሶስት

የመደምደሚያ ሀሳቦች

116. በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የግዥና ንብረት አስተዳደሩ በብቃት፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ በሆነ ሁኔታ እየተከናወነ መሆኑ ኦዲት በተደረገ ወቅት የሚከተሉት ዋና ዋና ግድፈቶች ተገኝተዋል፡-

- በረጅም ጊዜ ውል ግዥ ለመፈጸም የሚቻለው ምን አይነት ሁኔታዎች ሲሚሉ እንደሆነ በባንኩ የግዥ መመሪያ የማይገልጽ መሆኑ፣
- ባንኩ የግዥ ዕቅድ የሚያዘጋጅ ቢሆንም በዕቅዱ መሰረት አለመከናወኑ እና ዕቅድ አፈፃፀሙም ዝቅተኛ መሆኑ፣
- የግዥ ቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ (Procurement Specification) በተገቢው ባለሙያ ያልተዘጋጀላቸው ግዥዎች መኖራቸው እና ባንኩ ክፍያ ከመፈፀሙ እና ሙሉ ርክክብ ከማካሄዱ በፊት ዕቃዎችን (የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ) እና ተያያዥ አገልግሎቶችን በባለሙያ በምርምራና በሙከራ እንደማይረጋገጡ፣
- የንግድ ምልክት (ብራንድ) እየተጠቀሰ ጨረታ የሚወጣ መሆኑ፣
- ጨረታዎች ከወጡ በኋላ በተደጋጋሚ የሚሰረዙ መሆኑን፣
- ከባንኩ የግዥ መመሪያ በመተላለፍ ግዥዎች የሚፈጸሙ መሆኑን፣
- ለባንኩ ዕቃዎችንም ሆነ አገልግሎቶችን ለማቅረብ ውል ከገቡ በኋላ በውሉ መሰረት የማይፈፅሙ አቅራቢዎች ላይ በውሉ መሰረት አስተዳደራዊ እርምጃ የማይወሰድ መሆኑ፣
- ግዥዎች ከግዥ አጽዳቂ ቡድን ውጭ (በፕሮሰስ ካውንስሉ) እንዲጸድቁ የሚደረግ መሆኑ፣
- ባንኩ በየዓመቱ በከፍተኛ ገንዘብ የሚገዛቸው እቃዎች እንደተገዙ አገልግሎት ሳይሰጡ የሚበላሹበት ሁኔታ መኖሩ፣
- የተገዙ ንብረቶች ለሚመለከታቸው ተጠቃሚዎች ሳይሰራጩ የሚቆዩ መሆኑ፣
- በዲስትሪክት ወይም በቅርንጫፍ የሚገኙ ንብረቶች በኃላፊነት የሚረከቡት ሰራተኞችም ሆነ ስራ አስኪያጆች ባንኩን ሲለቁም ሆነ በዝውውር ምክንያት ሲሄዱ የተረከቧቸው ንብረቶች በትክክል ተቆጥረው የማያስረክቡ መሆኑን፣
- በባንኩ ያሉ ንብረቶች በመጋዘን ውስጥ ዝቅተኛና ከፍተኛ የዕቃ መጠን (Minimum and Maximum Stock Level) ያልተወሰነበት ሁኔታ መሆኑ፣
- የንብረቶች ጥገና በታቀደው መሰረት የማይከናወን መሆኑ፣

- በርካታ አገልግሎት የሚሠጡና የማይሰጡ ንብረቶች ተቀላቅለው በመጋዘን ውስጥ መቀመጣቸው እና ለፀሀይ፣ ለዝናብ፣ ለብክነት፣ ለብልሽት በተጋለጠ ሁኔታ ከመጋዘን ውጭ ተጥለው የተቀመጡ መሆኑ፣
- አገልግሎት አይሰጡም የተባሉ በርካታ የባንኩ ንብረቶች አገልግሎት ሊሰጡ ያልቻሉበት ምክንያት በባለሙያ በማስረጃ በተደገፈ ሁኔታ የማይረጋገጥ መሆኑ፣
- የባንኩ የንብረት አወጋገድ መመሪያ በ1999 ዓ/ም የወጣ ቢሆንም ከባንኩ ወቅታዊ ሁኔታ እና አሰራር ጋር እንዲጣጣም ተደርጎ ያልተከለሰ መሆኑ፣
- ባንኩ መወገድ የሚገባቸውን ንብረቶች በተመለከተ ዕቅድ የሌለው መሆኑ፣
- በባንኩ በዕዳ የተወረሱ ንብረቶች (Acquired Assets) ሳይሸጡ የቆዩ መሆናቸው እና በባንኩ ዋና መ/ቤት የሚደረግው ክትትልና ድጋፍ ጠንካራ አለመሆኑ፣
- በባንኩ የገበያ ጥናት ማከናወን አመላካች የዋጋ ዝርዝር (Indicative Price List) መዘጋጀት የሚገባ ቢሆንም የገበያ ጥናቱ ያልተከናወነ መሆኑ፣
- ባንኩ ያዘጋጀው የዕቃ አቅራቢዎች ዝርዝር በየጊዜው ወቅታዊ የማይደረግ መሆኑ፣
- ባንኩ የግዥ እና ንብረት አስተዳደርን በተመለከተ ማስረጃዎችን በዘመናዊ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሥርዓት በመጠቀም ያላደራጀ መሆኑ እና
- ወቅታዊ የሆነ ንብረቶችን በተመለከተ ቀልጣፋና ወጥ የሆነ የመረጃ ልውውጥ ከዲስትሪክቶችና ቅርንጫፎች አለመኖሩ

ታውቋል፡፡

117. ስለሆነም በኦዲቱ ወቅት የተገኙትን ድክመቶች እና ችግሮች ለማስወገድ ወይንም ለማቃለል አስተዋጽኦ ያደርጋሉ ብለን ያመንባቸውን የማሻሻያ ሃሳቦች በሚቀጥለው የሪፖርቱ ክፍል አቅርበናል፡፡

ክፍል አራት

የማሻሻያ ሀሳቦች

118. የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ያስቀመጠውን በ2025 በአለም ተወዳዳሪ የንግድ ባንክ የመሆን ራዕይ ለማሳካት የራሱን አስተዋፅኦ የሚያደርገው የግዥና ንብረት አስተዳደሩ ቀልጣፋ፣ ውጤታማና ስኬታማ በሆነ ሁኔታ እንዲከናወን እንዲሁም በቀጣይ በሚከናወኑ የስራ እንቅስቃሴዎች ላይ ተመሳሳይ ክፍተቶች እንዳይከሰቱ ያስችላሉ ያልናቸውን የማሻሻያ ሀሳቦች አቅርበናል፡-

- ባንኩ የግዥ ስርዓቱን ግልፅ ለማድረግ የረጅም ጊዜ ግዥ ውል የሚከናወኑ ግዥዎች የዕቃዎችን ዝርዝር ከማስቀመጥ ባለፈ በግዥ መመሪያው ላይ የሚቀመጡትን አሰራሮች ምን ምክንያቶች ወይም መስፈርቶች (ለዕለት ተዕለት ሥራ የሚገለግሉ፣ መደበኛ ጥገና ጋር የተያያዙ እና በአፋጣኝ የሚፈለጉ ንብረቶች የሚለዩበት) ሲሟሉ መከናወን እንዳለባቸው የመንግስት የግዥ አሰራርን መሰረት በማድረግ ሊያስቀምጥ እና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ባንኩ በየጊዜው ከሚያዘጋጀው የስትራቴጂክ ዕቅድ ጋር የተጣጣመ ራሱን የቻለ የግዥ ዕቅድ ሊያዘጋጅ፣ ይህንንም ዕቅድ ሲዘጋጅ ከየሥራ ክፍሎች ፍላጎት (በበጀት የተደገፈ) እና በመጋዘን ውስጥ ያሉ ክምችቶችን ግምት ውስጥ ሊያስገባ ይገባል፡፡ በተዘጋጀው የግዥ ዕቅድ መሰረትም ግዥዎቹ ሊከናወኑና ለየሥራ ክፍሎቹ በወቅቱ እንዲደርስ የሚያስችል አሰራር ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
- ባንኩ ግዥ ለመፈጸም የቴክኒካል ፍላጎት መግለጫ ዝርዝር (ስፔሲፊኬሽን) ለሚያስፈልጋቸው ዕቃዎች በባለሙያ ሊዘጋጅ እና ዕቃዎቹም ተገዝተው ሲመጡ ርክክብ ከመፈጸሙ በፊት በተጠየቀው የቴክኒክ ፍላጎት መሰረት መሆኑ ሊረጋገጥ እና የላብራቶሪ ፍተሻ ለሚስፈልጋቸው ዕቃዎች በሚመለከተው ክፍል ትክክለኛነቱን በማረጋገጥ ሊረከብ ይገባል፡፡
- ባንኩ ግልጽ እና ፍትሃዊ የግዥ ሥርዓት ተግባራዊ ለማድረግ በጨረታ ሰነድ ዝግጅት ወቅት የቴክኒካል ፍላጎት መግለጫ ዝርዝር (ስፔሲፊኬሽን) ሲዘጋጅ የአምራቾች የንግድ ምልክት (ብራንድ) እንዳይጠቀስ የሚደረግበት አሰራር በመዘርጋት ለብልሹ አሰራር እና ለሙስና የሚጋልጡ መንገዶችን መከላከል ይገባዋል፡፡

- ባንኩ ግዥዎችን ለመፈጸም ጨረታ ከማውጣቱ በፊት የግዥው አስፈላጊነት እና በቂ መግለጫ የያዘ የጨረታ ሰነድ ሊያዘጋጅ፣ በተያዘለት የጊዜ ገደብ ሊከናወንና ዕቃዎቹ ሆነ አገልግሎቶቹ ለሚፈለግባቸው ተግባር እንዲውሉ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ባንኩ የሚያከናውናቸው ግዥዎች ሁሉ በግዥ መመሪያው ላይ በተቀመጡት የግዥ ዘዴዎች፣ መስፈርቶች ወይም/እና የገንዘብ ጣሪያ መሰረት ውድድርን መሰረት በማድረግ እንዲከናወኑ በማድረግ ለብልሹ አሰራር የሚያጋልጡ ሁኔታዎችን ሊያስወግድ እና ያወጣቸው ህጎች ተግባራዊ መሆናቸውን የሚያረጋግጥበት ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ግዥዎች በመመሪያው ላይ እንዲያጸድቁ ሥልጣን እና ኃላፊነት በግልጽ ከተሰጣቸው የሚመለከታቸው ኮሚቴዎች ውጭ እንዳይጸድቁ በማድረግ ግልጽነት እና ተጠያቂነት ያለው አሰራርን በማጠናከር ሁሉንም ግዥዎች ሊያከናውን ይገባል፡፡
- ባንኩ በሚያከናውናቸው የእቃ፣ የአገልግሎትም ሆነ የግንባታ ግዥዎች ላይ አቅራቢ ድርጅቶች በገቡበት የጊዜ ገደብ መሰረት ዕቃውን፣ አገልግሎቱንም ሆነ ግንባታውን በማቅረብ ለተጠቃሚው አካል በወቅቱ እንዲደርስ በማያደርጉ አቅራቢዎች ላይ ባንኩ በውሉ መሰረት የራሱን መብት ሊያስከብር እንዲሁም እንደአስፈላጊነቱ አስተዳደራዊ እርምጃ (ከአቅራቢነት እስከማገድ ድረስ) ሊወስድ ይገባል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ ግዥዎች ላይ በሚከናወኑ የውል አፈፃፀሞች ላይ ባንኩ የራሱን የክትትልና ቁጥጥር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ባንኩ በግዥ መመሪያው መሰረት በተቋቋሙት የግዥ አጽዳቂ ቡድኖች ብቻ የግዥ ግምገማዎችን በማወዳደር እንዲጸድቁ በማድረግ የባንኩ የበላይ ኃላፊዎች የሚቀርቡ ቅሬታዎችን መፍትሄ እንዲያገኙ ሊያደርጉ ይገባል፡፡
- የተገዙ ዕቃዎችን በግዥ ዕቅዱ በቀረበው ፍላጎት መሰረት ለተለያዩ የሥራ ክፍሎች፣ የዲስትሪክትና የቅርንጫፎችን የግዥ ፍላጎትና ጥያቄ መሰረት በማድረግ ንብረቶችን በወቅት እንዲሰራጩ እና ሥራ ላይ እንዲውሉ ሊያደርግ እና ተግባራዊነቱን ለመከታተል የሚያስችል የክትትል ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

- የባንኩ ሰራተኞች ንብረትን በስማቸው እንዲረከቡ በማድረግ ስራ ሲለቁ የተረከቡትን ማንኛውም ንብረት ለባንኩ ገቢ ማድረጋቸውን የሚከታተልበት የተጠናከረ የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- መጠገን የሚገባቸው የባንኩ ንብረቶች ውጤታማ በሆነ መልኩ ተጠግነው ጥቅም ላይ እንዲውሉ እንዲሁም የታቀደ ዕቅድ ተግባራዊ እንዲሆን በራሱ ባለሙያዎችም ሆነ አገልግሎቱን በመግዛት ቀልጣፋና ውጤታማ የሆነ የጥገና አሰራር ስርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ በማድረግ የተበላሹት በፍጥነት ሥራ ላይ እንዲውሉ ማድረግ አለበት፡፡
- ባንኩ በዕቅድ የሚገዛቸው ካፒታል እና ኦፕሬሽናል ዕቃዎች ሳይባክኑና የመገልገያ ጊዜያቸው ሳያልፍ በአግባቡ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ለንብረቶች እንደ የባህሪያቸው ዓይነት ዝቅተኛና ከፍተኛ የዕቃ መጠን (Minimum and maximum stock level) ወስኖ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ባንኩ የሚያገለግሉና የማያገለግሉ ንብረቶች በተለያየ መጋዘን ተደራጅተው እንዲሁም ንብረቶች እንደየአይነታቸው ተለይተው ማስቀመጥ የሚያስችል የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ የማያገለግሉ ንብረቶች ተጠግነው ሥራ ላይ የማይውሉት በሚመለከታቸው ባለሙያዎች እየተረጋገጠ በዕቅድ ላይ ተመስረቶ የሚወገዱበት አሰራር ዘርግቶ ተግባራዊ በማድረግ የማያገለግሉ ንብረቶችን ክምችት ሊቀንስ ይገባል፡፡ በተጨማሪም ባንኩ ያዘጋጀውን የንብረት አወጋገድ መመሪያ ወቅታዊ በማድረግ ሊያሻሽለው ይገባል፡፡
- ባንኩ በየክልሉ የሚገኙና በዕዳ የተወረሱ ንብረቶቹን በተሟላ ሁኔታ መረጃቸውን በመያዝ በምን ሁኔታ እንዳሉ ለማውቅ እንዲያስችለው ክትትልና ቁጥጥር የሚያደርግበትና የሚያስታርቅበት አሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ባንኩ ለሚያደርጋቸው ግዥዎች የዋጋ ማስተካካያዎችን ለማድረግ እንዲያግዝ በመደበኛነትና ወቅታዊነቱን በጠበቀ ሁኔታ የገበያ ጥናት በማከናወን የዕቃዎች ዋጋ ዝርዝርን ወቅታዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ በተጨማሪም ባንኩ ያዘጋጀውን የዕቃ አቅራቢዎች ዝርዝር በየጊዜው ወቅታዊ ሊያደርገው ይገባል፡፡
- ባንኩ የሚያከናውናቸው ግዥዎች ጥራታቸውን የጠበቁና ከትክክለኛ አቅራቢ የሚገዙ እንዲሆኑ፣ አዳዲስ አቅራቢዎችን ለማካተት እንዲሁም በተለያየ ምክንያት

ከስራ ዘርፋቸው እንዲገለሉ የተወሰነባቸውን አቅራቢዎች እንዳያቀርቡ ለመከላከል እንዲቻል ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በጋራ በመሆን የአቅራቢዎች ዝርዝር በማዘጋጀትና በማፀደቅ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

- ባንኩ ዲስትሪክቶች እና ቅርንጫፎች ስለያዙት ንብረት ወቅታዊና የተሟላ መረጃ ለዋና መ/ቤቱ በየወሩ እንዲልኩ የሚያችል አሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማደረግ እንዲሁም ባንኩ በግዥና ንብረት አስተዳደር ዙሪያ ያለውን ሙሉ መረጃ በየጊዜው ወቅታዊ በማድረግ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ በመታገዝ በማደራጀትና የግዥና ንብረት መረጃ ልውውጥ ሥርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

119. በመጨረሻም በኦዲቱ ወቅት በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ዋና መ/ቤት በግዥና ንብረት አስተዳደሩ ላይ ያሉ፣ በናሙና የታዩ ዲስትሪክቶችና ቅርንጫፍ መ/ቤቶች ኃላፊዎች እና ሠራተኞች ላደረጉልን የሥራ ትብብር እናመሰግናለን፡፡

አባሪ 1 የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative Criterias)

ተ.ቁ	የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues)	የኦደት መመዘኛ መስፈርቶች(Evaluative Criterias)
1.	የባንኩ የግዥ አፈፃፀም ወጪ ቆጣቢ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑን መገምገም	1. የመንግስት የግዥ መመሪያን መሰረት በማድረግ ባንኩ የራሱን የግዥ መመሪያ ሊያወጣና በሚመለከተው አካል በማፀደቅ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
		2. ባንኩ የግዥ ስትራቴጂክ ዕቅድ ሊያዘጋጅ እና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
		3. ባንኩ የሩብ ዓመት፣ የግማሽ ዓመት እንዲሁም የዓመት በሚል ከፋፍሎ የግዥ ዕቅድ ሊያዘጋጅና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
		4. ባንኩ በዕቅዱ መሰረት ግዥ ለመፈፀም እንዲቻል የግዥ ፍላጎት በግዥ ዕቃዎች አይነት፣ ብዛት እና የጥራት ደረጃ ከየቅርንጫፉ ሊሰበስብ ይገባል፡፡
		5. ባንኩ ለሚገዛቸው ለእያንዳንዱ ግዥዎች የግዥ ቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ (Procurement Specification) በባለሙያ ሊዘጋጅና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
		6. ባንኩ ለሚገዛቸው ለእያንዳንዱ ግዥዎች የግዥ ቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ (Procurement Specification) የሚያዘጋጅ እና የቴክኒክ ግምገማ (Evalution) የሚያደርግ ባለሙያ እንዲለያይ ሊያደርግ ይገባል፡፡
		7. ባንኩ ለሚፈፅማቸው ግዥዎች አስገዳጅ ሁኔታ ከሌለ በስተቀር በግልፅ ጨረታ ሊያከናውን ይገባል፡፡
		8. አቅራቢው ወይም አገልግሎት ሰጪው ከባንኩ ጋር በገባው ውል መሰረት ዕቃውን ካላቀረበ ወይም አገልግሎቱን ካልሰጠ ባንኩ በውሉ መሰረት ሕጋዊ መብቱን ሊያስከብር ይገባል፡፡
		9. ግዥ የማፅደቅ ስራ በግዥ አፅዳቂ ቡድን ብቻ ሊፈፀም ይገባል፡፡
		10. የግዥ አፅዳቂ ቡድን የጨረታውን አከፋፈት ሂደት ቃለ ጉባኤ መያዝ አለበት፡፡
		11. ባንኩ ክፍያ ከመፈፀሙ እና ሙሉ ርክክብ ከማካሄዱ በፊት ዕቃዎችን (የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ) በባለሙያ በምርምራና በሙከራ ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡
2	የባንኩ ንብረት አስተዳደር ወጪ ቆጣቢ ውጤታማና ቀልጣፋ መሆኑን መገምገም 2.1 የንብረት አያያዝ እና አጠቃቀም ስርዓት መኖሩንና ተግባራዊ መሆኑን መገምገም	12. የመንግስትንብረት አስተዳደር መመሪያን መሰረት በማድረግ ባንኩ የራሱን የንብረት አስተዳደር መመሪያ ሊያወጣና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
		13. በባንኩ የተገዙ ዕቃዎች የግዥ ጥያቄ ላቀረበው ክፍል ወይም ቅርንጫፍ በወቅቱ ሊሰራጩ ይገባል፡፡
		14. ሁሉም የባንኩቋሚ ዕቃዎች መለያ ቁጥር (Alpha Numerical coding) ሊሰጣቸው እና ሊመዘገቡ ይገባል፡፡
		15. በተለያየ ምክንያት ስራ የሚለቁ የባንኩ ሰራተኞች በስማቸው የተመዘገቡትን ቋሚ ንብረቶች እንዲያስረክቡ የቁጥጥር እና የክትትል ስርዓት ሊኖርና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
		16. ለባንኩ ንብረቶች ጥገና የሚደረግበት የአሰራር ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
		17. ባንኩ መጋዘን ውስጥ ለሚያስቀምጣቸው ንብረቶች እንደየባህሪያቸው ዓይነት ዝቅተኛና ከፍተኛ የዕቃ መጠን (Minimum and maximum stock level) ተወስኖ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
		18. የሚያገለግሉና የማያገለግሉ የባንኩ ንብረቶች ተለይተው

		የሚቀመጡበት የአሠራር ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
		19. አገልግሎት አይሰጡም ተብለው የሚቀመጡ የባንኩ ንብረቶች አገልግሎት ሊሰጡ ያልቻሉበት ምክንያት በባለሙያ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡
		20. ባንኩ በዕዳ የተያዙ ንብረቶችን በውርስ የራሱ ለማደረግ ሲወስን የባለቤትነት መብቱን በፍጥነት ለማዘዋወር የሚስችለው የአሰራር ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
		21. በብድር የተያዙ ንብረቶችን በአግባቡ ስለመያዛቸው ክትትል የሚደረግበትና ሪፖርት የሚቀርብበት የአሰራር ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
		22. ባንኩ በተለያየ ሥፍራ የሚገኙትን (የዋናው መስሪያ ቤትና ዲስትሪክት ቢሮዎች) በዕዳ የተያዙ ንብረቶቹን በቆጠራ ከተገኘው የቋሚ ንብረት መዝገብ ጋር በዓመት ሁለት ጊዜ ማስታረቅ ይኖርበታል፡፡
	2.2 **የንብረት አወጋገድ ስርዓት መኖሩንና ተግባራዊ መሆኑን መገምገም**	23. አገልግሎት የማይሰጡ የባንኩ ንብረቶች የሚወገዱበት የአወጋገድ ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
		24. የተወገዱ የባንኩ ንብረቶች ከመዝገብ ሊሰረዙ (Write-Off) ይገባል፡፡
		25. ባንኩ የሚያስወግዳቸው ንብረቶች የሚወገዱበትን መንገድ (በሽያጭ፣ በስጦታ እና በውዳቂ) የተወሰነበትን ምክንያት በግልፅ ሊያስቀምጥ ይገባል፡፡
3	**የባንኩ የግዥና ንብረት አስተዳደርን በተመለከተ የመረጃ አያያዝ ስርዓትና በዘርፉ ለተሰማሩ ሰራተኞች የስልጠና ስርዓት መኖሩን መገምገም**	ባንኩ ለሚያከናውናቸው ግዥዎች መደበኛ የሆነ የገበያ ጥናት ማከናወን አለበት፡፡
		27. ባንኩ በግዥ ስራ እና በግዥ አጽዳቂነት እንዲሁም በንብረት አስተዳደር ለተመደቡ ሰራተኞች መንግስት ያወጣውን የግዥና ንብረት አስተዳደር የሚመለከቱ አዋጅ፣ መመሪያዎች እና አሰራሮች በእቅድ ላይ የተመሰረተ እና ወጥነት ያለው ስልጠና ሊሰጣቸው ይገባል፡፡
		28. ባንኩ የአቅራቢዎችን የብቃት ደረጃ በመለካት የአቅራቢዎች ዝርዝር በመከለስ ለሚመለከታቸው አካላት አቅርቦ በማፀደቅ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
		29. ቅርንጫፎችና ዲስትሪክቶች ስለባንኩ ንብረቶች ሙሉና ወቅታዊ መረጃ ለዋናው መስሪያ ቤት በየወሩ ሊልኩ ይገባል፡፡
		30. ባንኩ የግዥ እና ንብረት አስተዳደርን በተመለከተ ማስረጃዎችን በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሊያደራጅ ይገባል፡፡

አባሪ 2፡ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ድርጅታዊ መዋቅር



አባሪ 3፡ ማስረጃ ያላሟሉ ተጫራቾችን የሚያሳይ ሰንጠረዥ

የተገዙ የዕቃ አይነቶች	ከ2006-2008 ዓ/ም የታዩ የጨረታ ሰነዶች	ተጫራቾች የጨረታ ሰነድ ሲገዙ ማሟላት የሚገባቸውን ማስረጃዎች በተመለከተ			በየጨረታ ቁጥሩ ማስረጃ ሳያያይዙ አሸናፊ የሆኑ ተጫራቾች ብዛት	የጨረታ ኮሚቴ በሚያከናውነው የጨረታ ሂደት የሚያዝ ቃለ ጉባኤ	የአይቲ ዕቃዎች ወደ መጋዘን ሲገቡ ምርመራ መደረጉን
		በከፊል ያሟሉ ተጫራቾች ብዛት	ሙሉ በሙሉ ያላሟሉ ተጫራቾች ብዛት	ፋይናንሻል እና ኦዲት ሪፖርትን በተመለከተ			
IT Equipment	39/2014/15	4	6	አልተያያዘም	አንድ አሸናፊ	-	አልተደረገም
	01/2014/15	-	16	አልተያያዘም		-	አልተደረገም
	05/2014/15	7	6	አልተያያዘም	አንድ አሸናፊ	-	-
	21/2014/15	-	15	አልተያያዘም	አንድ አሸናፊ	-	-
	64/2014/15	12	5	አልተያያዘም		የለም	-
	55/2014/15	11	15	አልተያያዘም	አንድ አሸናፊ	-	-
	23/2013/14	20	7	አልተያያዘም		የለም	-
	44/2013/14	41	3	አልተያያዘም		የለም	-
	04/2015/16	14	7	አልተያያዘም		-	-
	07/2015/16	6	10	አልተያያዘም	አንድ አሸናፊ	-	-
	34/2015/16	1	17	አልተያያዘም		-	-
	29/2015/16	-	4	አልተያያዘም		-	አልተደረገም
	24/2014/15	4	4	አልተያያዘም		የለም	አልተደረገም
	20/2014/15			አልተያያዘም		የለም	አልተደረገም
	43/2014/15	5	18	አልተያያዘም		-	-
	72/2013/14	8	8	አልተያያዘም	ሁለት አሸናፊዎች	-	አልተደረገም
	50/2013/14	7	3	አልተያያዘም	ሁለት አሸናፊዎች	-	ለ1 አቅራቢ ብቻ ምርመራ የተደረገ መ ሆኑ
	57/2013/14	20	7	አልተያያዘም		-	-
	33/2013/14	11	9	አልተያያዘም		የለም	አልተደረገም
	03/2015/16	1	4	አልተያያዘም	አንድ አሸናፊ	-	አልተደረገም
	42/2013/14	10	4	አልተያያዘም	አንድ አሸናፊ	-	ከአንዱ ዕቃ በቀር ለሌሎቹ ምርመራ አልተደረገም
	14/2015/16	6	5	አልተያያዘም	ሶስት አሸናፊዎች	-	አልተደረገም
	17/2014/15	10	4	አልተያያዘም	ሁለት አሸናፊዎች	-	-
	26/2014/15	4	20	አልተያያዘም	ሶስት አሸናፊዎች	የለም	ከአንዱ ዕቃ በቀር ለሌሎቹ ምርመራ አልተደረገም
	03/2013/14	35	-	አልተያያዘም	ሁለት አሸናፊዎች	-	ከአንዱ የአይቲ ዕቃ በቀር ለሌሎች ምርመራ ያልተደረገ
Office	25/2014/15	35	12	አልተያያዘም		የለም	አልተደረገም

Equipment	04/2014/15	5	12	አልተያያዘም	ሁለት አሽናፊ	-	-
	03/2014/15	6	9	አልተያያዘም		-	አልተደረገም
	22/2015/16	-	22	አልተያያዘም	አንድ አሸናፊ	-	-
	33/2015/16	5	23	አልተያያዘም		-	-
	23/2015/16	2	11	አልተያያዘም		የለም	-
	12/2015/16	4	13	አልተያያዘም		-	-
	73/2014/15	8	11	አልተያያዘም	አንድ አሸናፊ	የለም	-
	16/2014/15	4	24	አልተያያዘም	ሁለት አሸናፊዎች	-	-
	15/2014/15	10	17	አልተያያዘም	-	-	-
	28/2014/15	1	9	አልተያያዘም	-	የለም	-
	63/2013/14	6	3	አልተያያዘም	-	-	-
	45/2013/14	13	11	አልተያያዘም	-	የለም	
	16/2013/14	14	35	አልተያያዘም	-	የለም	-
	52/2013/14	2	2	አልተያያዘም	-	የለም	-
	62/2013/14	6	4	አልተያያዘም	-	የለም	-
	61/2015/16	7	13	አልተያያዘም	-	-	-
	53/2014/15	18	8	አልተያያዘም	-	የለም	-
Furniture & Fittings	52/2014/15	2	8	አልተያያዘም	-	-	-
	01/2013/14	19	28	አልተያያዘም	-	-	-
	09/2015/16	-	10	አልተያያዘም	ሶስት አሸናፊዎች	-	-
	26/2015/16	4	9	አልተያያዘም	-	-	----
	13/2014/15	13	16	1 አቅራቢ ብቻ ያቀረበ	አራት አሸናፊዎች	የለም	-
	08/2014/15	12	25	አልተያያዘም	አራት አሸናፊዎች	የለም	-
E-Payment	10/2014/15	10	8	አልተያያዘም	-	-	-
	24/2013/14	18	5	አልተያያዘም	-	የለም	-
	64/2013/14	-	3	አልተያያዘም	-	የለም	-
	44/2015/16		4	አልተያያዘም	-	-	
	43/2013/14	7	2	አልተያያዘም	-		
Vehicle	19/2013/14	-	8	አልተያያዘም	አንድ አሸናፊ	የለም	-
	77/2013/14	-	6	አልተያያዘም	-	የለም	-
	18/2015/16	-	5	አልተያያዘም	አንድ አሸናፊ	የለም	-
	67/2014/15	-	8	አልተያያዘም	-	የለም	-
	78/2014/15	-	8	አልተያያዘም	-	-	
Service	49/2015/16		4	1 አቅራቢ ብቻ ያያዘ	-	የለም	
	Supplier list 2007 ዓ.ም	1	22	አልተያያዘም	-	የለም	
Drugs& Laboratory Equipment	ሚያዚያ 1 2008	-	12	አልተያያዘም	-	የለም	-
	February 20 2014	11	6	አልተያያዘም	-	የለም	-
	መጋቢት 2007	3	-	አልተያያዘም	-	የለም	
	ሚያዚያ 20 /04/15	8	-	አልተያያዘም	-	የለም	-
	09/10/2014	8	9	አልተያያዘም	-	የለም	-
	ነሐሴ 2007	2	1	አልተያያዘም	-	የለም	-
	July 07 /2015	4	9	አልተያያዘም	-	የለም	-

	መስከረም 2008	2	7	አልተያያዘም	-	የለም	-
	14/01/2016	3	9	አልተያያዘም	-	የለም	-
Constricti on							-
	ጎንደር ቅርንጫፍ ግንባታ	አፍሮ ፂዮን እና አባኮ የተባሉ ድርጅቶች ካለ ምንም ጨረታ አሸናፊ መሆናቸው	ተጫቾቹ በውስጥ ባሉ ባለሙያዎች አስተያየት የመጡ መሆናቸው	አልተያያዘም	ሁለት አሸናፊዎች	የለም	-

አባሪ 4፡ የአሰራር ስርዓት ስዕላዊ መግለጫ



አባሪ 5፡ በቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ (ስፔስፊኬሽን) መሰረት ስለመሆናቸው በተገቢው ባለሙያ ስለመረጋገጡ የሚያስረዳ ማስረጃ ያልቀረበላቸው ግዥዎች

ተራ ቁ.	የጨረታ ሰነድ ቁጥር	የገንዘቡ መጠን በብር
1	72/2013/14	295,105.53
2	50/2013/14	7,660,492.00
3	33/2013/14	11,696,400.00
4	42/2013/14	2,813,039.15
5	03/2013/14	76,143,318.94
6	39/2014/15	1,009,600.00
7	01/2014/15	48,085,087.05
8	24/2014/15	309,812.30
9	20/2014/15	15,923,715.00
10	26/2014/15	13,579,551.04
11	25/2014/15	27,299,517.04
12	03/2014/15	10,806,180.00
13	29/2015/16	498,268.92
14	03/2015/16	1,183,988.52
	ድምር	217,304,075.49